# አርነት በእውነት

## በኢትዮጵያ የቤተክርስቲያን ታሪክና ታሪካዊ ሥነ መለኮት ላይ ያተኮረ

*«ኢየሱስም ... እናንተ በቃሌ ብትኖሩ በእውነት ደቀ መዛሙርቴ ናችሁ፤*
*እውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣችኋል አላቸው፡፡»*

*የሐ. 8:31-33*


በ

**በልሁ ደሰለኝ**

አርታይ፡- ደረጀ በቀለ



ራዕይ አሳታሚ
አዲስ አበባ 1998 ዓ.ም.

# አርነት በእውነት

ይህንን መጽሐፍ ያለ አሳታሚው ፈቃድ ማባዛት
ወይም እንደገና ማሳተም በሕግ የተከለከለ ነው።

ራዕይ አሳታሚ
የፖ. ሳ. ቁ 2332
አዲስ አበባ

RP-18

ዝክረ ስማዕታት ወሰባክያነ ወንጌል

*ይህች መጽሐፍ የወንጌልን እውነት በምድራችን በኢትዮጵያ ለሙድ ለማስተሳሰር መሰዋዕትነትን ለከፈሉ ለአባቶች መታሠቢያ በየዘመናቱ ቤተክርስቲያን ስትሰት ወደ እግዚአብሔር የስድኅናት ወንጌል እንድትመለስ እግዚአብሔር ኀትዓች ለድርገ እያዕነሳቸው ሳሉተም ማስታወሻ ትሁንልኝ!!!*

3.1.4. ኃጢአትና ድነት በተዋሕዶ ግንዛቤ - - - 110
3.1.4.1. ስለ ኃጢአት ምንነት ግንዛቤዋ 110
3.1.4.2. ስለ ድነት ያላት ግንዛቤ- - - - 112
3.1.4.3. እውነትን የሸፈነው አመድ ይርገፍገፍ! - - - - - - - - --113
3.1.4.4. እንማማር - - - - - - - - - - 117
3.1.5. ቤተ ክርስቲያን በተዋሕዶ ግንዛቤ - - - - -120
3.1.5.1. ስለ ቤተ ክርስቲያን ማንነት ያላት ግንዛቤ - - - - - - - - - - - - -120
3.1.5.2. የቤተ ክርስቲያን ተከላ ስልቶቿ121
3.1.5.3. እንማማር - - - - - - - - - - 122
3.1.6. ምጽዓተ ክርስቶስና የዓለም ፍጻሜ በተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን - - - - - - - - - - - - - 124
3.1.6.1. ምጽዓታዊ እሳቤዎች በኢትዮጵያ 124
3.1.6.2. እንማማር - - - - - - - - - - 126
3.2.የተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያንና ቅዱሳት ሥርዓቶቿ - - - -127
3.2.1. ትዕዛዛዊ መመሪያ ያላቸው ሥርዓቶች- - - -127
3.2.1.1. ጥምቀት - - - - - - - - - - - - - -127
3.2.1.2. ቁርባን - - - - - - - - - - - - - - -128
3.2.2. ትረካዊና በውርስ የተገኙ ሥርዓቶች - - - -129
3.2.2.1. ሜሮን - - - - - - - - - - - - - - 130
3.2.2.2. ሢመት (ክህነት) - - - - - - - - - -130
3.2.2.3. ተክሊል - - - - - - - - - - - - - -132
3.2.2.4. ንስሐ - - - - - - - - - - - - - - -132
3.2.2.5. ቀንዲል - - - - - - - - - - - - - 133
3.2.3. እንማማር - - - - - - - - - - - - - - 134

3.3.ኦርቶዶክሳዊነት ሀገር በቀል ወይስ መጤ? - - - - - - -135
3.3.1. ኦርቶዶክሳዊነትና የብሉይ ኪዳን እንዲሁም የዕብራውያን ባህል ተጽዕኖ በኢትዮጵያ - - - - - -137
3.3.2. ኦርቶዶክሳዊነትና የአረማዊነት ተጽዕኖ በኢትዮጵያ - - - - - - - - - - - - - - - -139
3.3.3. እንማማር - - - - - - - - - - - - - - - - -141
ማጠቃለያ - - - - - - - - - - - - - - - - - - - - - - 146
ዋቢ መጻሕፍት - - - - - - - - - - - - - - - - - - - - - - 148

## መግቢያ

ከሀገራችን አባባሎች መካከል አንዱ፡- «እውነትና ንጋት እያደረ ይጠራል!!» የሚል ነው፡፡ እውነት በተለያየ ምክንያት ትሸፈን ይሆን እንጂ አትጠፋም፡፡ እውነትን ከሚጋርዷት መካከል በጊዜ ርዝመት ውስጥ እርሷን የሸፈነ እውነት መሳይ ግን በምንነቱ ከእውነት የዳለጠ የታሪክ ዘገባ ነው፡፡

በምድራችን በኢትዮጵያ ከታሪካችን የምናስተውለውም ይህንኑ ነው፡፡ ከምንከራባቸው ታሪኮቻችን አንዱ ቅኝ ግዛትን ያላስተናገድን መሆናችን ሲሆን ከዚህም ጋር በተያያዘ በኃይማኖት ረገድም ወንጌልን ከምንጩ መቀበላችንም እንዲሁ፡፡ ታዲያ በሃዋርያት የተሰበከው ወንጌል በምድራችን እንደዚያው በትኩስነቱ አለ ማለት የማያስደፍረን ታሪካችንን ስንቃኝና ከቅዱስ ቃሉም ስናመሣክር ነው፡፡

አኩሪ ታሪካችን በራስ መተማመንን አጎልብቶልን ሃገር በቀል ልንል በምንችለው መልኩ የነገረ መለኮት አጎለባበት አብቅቶናል፡፡ ስለዚህም በሌላው የክርስቲያን ዓለም የማይስተዋል አስተምህሮት እና ልምምድ በኢትዮጵያ ክርስትና ላይ ተንጸባርቋል፡፡ ይህም ደግሞ እንደ ጥንታውያን የአረማዊነትና የዕብራውያን ትምህርትና ልምምድ÷ በጉዲትና በመሃመድ ግራኝ ዘመን የተከሰቱ ከቃለ እግዚአብሔር ያፈነገጡ የባህል ወረራዎች እንዲሁም እንደ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ባሉ ነገሥታትም ዘመን በተከሰተ የቀኖና ልቅነት ለበርካታ «የተገለጠልኝ ባይ» ድርሰቶች መጋለጥንንም ያካትታል፡፡ ታዲያ ከአኩሪው ታሪካችን በስተጀርባ «ባህል ሲቆይ ሃይማኖት ይሆናል!» እንዲሉ በምድራችን የወንጌልን እውነት የሸፈኑና አርነትን ያሳጡን የታሪክ ጠባሳዎች በክርስትና ስም ተንሰራፍተዋል፡፡



እውነት መዳፈን መቻሉ እያደር ያዳፈነውን አመድ አራግፎ የመውጣቱን ተስፋ ይፈነጥቃል፡፡ ይህ ደግሞ ከምዕራቧም ሆነ ከምሥራቋ ቤተክርስቲያን ታሪክ እንደምንረዳው ብዙዎች ለማዕት የሆኑበትና እየሆኑለትም ያሉ መሆናቸውን ምሥክር ያደርገናል፡፡ በእኛም ሀገር ብዙዎች መሥዋዕት ሆነውለታል! እውነትም ብዙዎችን አርነት እያወጣና በማውጣትም ላይ የመሆኑ ታሪክ እስከ ጌታችን ዳግም ምጽዓት የሚቀጥል ነው፡፡

ስለዚህም ይህች በኢትዮጵያ የቤተክርስቲያን ታሪክና ታሪካዊ ሥነ መለኮት ላይ ያተኮረች መጽሐፍ ታሪካችንንና የሥነ መለኮት አጎለባበትን በማስቃኘት ከታሪክ በምንማርበት መንገድ ላይ ትኩረት በማድረግ እንዲሁም ለምናስተውላቸው ወንጌል ያልዳሰሳቸው ልምምዶች በምክንያትነት የሚጠቀሱትንም የታሪክና የአስተምህሮ ጠባሳዎች ግንዛቤ በማስጨበጥ እውነተኛ ተሃድሶ በማምጣት ለእውነተኛ አርነት ምክንያት ትሆነን ዘንድ አበረክታለሁ፡፡ ስለ መጽሐፍ ማንኛውንም አስተያየታችሁንና ጥያቄዎቻችሁን በአድራሻዬ መላክ ትችላላችሁ፡፡

በልሁ ደለለኝ

ሚያዝያ 1998 ዓ/ም

## I. ከታሪካችን የምንማማረው

## 1.1. ቅድመ ክርስትና:- ጥንታዊት ኢትዮጵያና እምልኮዋ

የሰው ዘር አንድ እንደሆነ መጽሐፍ ቅዱስ በግልጽ ያስተምረናል (ኦሪት ዘፍጥረት 1:26-28፤ሐዋ. 17:26-27):: ከእግዚአብሔር የባርኮት ቃል የተነሣም የሰው ዘር በዝቶ ዓለምን ወርሷል (ዘፍ. 1:28):: በአሁኑ ወቅት የዓለም ሕዝብ ብዛት 6.2 ቢልዮን ደርሷል:: የእያንዳንዱ ሕዝብ ታሪክ ደግሞ በማንነቱ ላይ ከሚደረግ ጥናት ይጀምራል:: ስለዚህም የኢትዮጵያን ሃይማኖታዊ ገጽታ መዳሰስ ከመጀመራችን በፊት በኢትዮጵያ ያሉትን ብሔር ብሔረሰቦች ማንነትና መልክዓ ምድራዊ አሠፋፈር ላይ የተደረጉ ጥናቶችን ጥቂት መመልከቱ አስፈላጊ ነው::

### 1.1.1. የኢትዮጵያውያን ማንነት ታሪክ

በኢትዮጵያ ምድር የመጀመሪያዎቹ ሰፋሪዎች እንደሆኑ የሚነገርላቸው ከኖኅ ልጆች የካም ልጅ የኩሽ ዘሮች ናቸው (ዘፍ 6: 10፤ 10:6):: የአዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ የመልክዓ ምድር ምሑራን *Introductory Geography of Ethiopia* በተባለው መጽሐፍ ስለ ኢትዮጵያ ሕዝቦች ያደረጉትን ገለጻ ከዚህ እንደሚከተለው ለማስፈር እሞክራለሁ[1]:-

[1] Beyene Dolicho (Dr.), *Introductory Geography of Ethiopia*, Addis Ababa, **AAU Department** of Geography, pp. 90-91



ኩሻዊነት የኢትዮጵያውያን መለያ ከመሆኑ የተነሣም "ፕሮቶ ኢትዮጵያንስ" /Proto-Ethiopians/ ተሰኝቷል:: ኩሽ የሚለው የዕብራይስጥ ስያሜ በሰባ ሊቃውንት ወደ ግሪክ ቋንቋ እንደተመለሰ በሚነገርለትና ሰፕትዋጅንት በመባል የሚታወቀው የግሪክ ብሉይ ኪዳን ኢትዮጵያ ተብሎ ተተርጉሟል:: ኩሽ የናይል ሸለቆን፤ ደቡብ ግብፅን፤ ኑብያን (ሱዳን) እና አቢሲንያን የሚያካትት ስፍራ ነው:: ይህም በዘፍጥረት 2:13 የተገለጸውን ትክክል ያስኘዋል:: እነዚህ ኩሻይቶች "ፕሮቶ ኢትዮጵያን" /Proto-Ethiopians/ በ2000 ዓ.ዓ. ገደማ በአራት ቋንቋዎችና የራሳቸው ባህል ያላቸው ሕዝቦች ሆነው በቡድን ተደራጁ::

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በአፍሮ ኤሽያቲክና በናይሎ ሰሃራ (Nilo-Saharan) በሁለት ታላላቅ የቋንቋ ቤተሰብ ሥር ይመደባሉ:: የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ በአፍሮ ኤሽያቲክ (Afro-Asiatic) ፤ሌሎቹ ደግሞ በናይሎ ሰሃራ (Nilo-Saharan) ቋንቋነት ይታወቃሉ::

የአፍሮ-ኤሽያቲክ (Afro-Asiatic) የቋንቋ ቤተሰብ በመባል ከሚታወቁት ሦስቱ ውስጥ ኩሻውያን አንዱ ሲሆኑ ይህም በርካታ ቋንቋዎችን የሚያካትት ነው:: ከእነዚህ ውስጥ ኦሮምኛ÷ ሶማልኛ÷ ሲዳምኛ÷ ከምባትኛ÷ ሐድይኛ÷ አላብኛ÷ አፋርኛ÷ ጌድዮኛ÷ በስንኛና ሳሆኛ ይገኝ-ብታል:: በመልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ላይ በመመርኮዝ ባላቸው አሰፋፈርም ረገድ የመጀመሪያዎቹ *ሰሜናዊ ኩሻውያን* በጌዎች /Bejas/ በመባል የሚታወቁ ሲሆኑ በጥንት ግሪኮች ዘንድ በልሚያ /Blemmya/ ይባላሉ:: እነርሱም በሰሜናዊ ኤርትራና ደቡባዊ ሱዳን የሚኖሩ ሲሆን ኑሮአቸው የተመሠረተውም በዘላንነት (በከብት እርቢነት) ነው::

በጌምድር በመባል ይጠራ የነበረው የኢትዮጵያ ግዛትም ቤጃ-ምድር /Beja-Mider/ በግዕዙ የቤጃዎች ምድር ወይም የቤጃዎች መኖሪያ ማለት ነው:: ሁለተኛው ደግሞ ማዕከላዊ ኩሻውያን በመባል የሚታወቁና የአገው ሕዝቦች ሲሆኑ ኑሮአቸው በጥራጥሬ ምርትና በእንስሳት ርባታ ላይ የተመሠረተ ነበር::

ሦስተኛዎቹ ደግሞ ምዕራባዊ ኩሻዊያን በመባል የሚታወቁ የሳሆ፣ ኦሮሞ፣ ሶማሌና ሲዳማ ሲሆኑ ኑሮአቸው በጥራጥሬ እህል ምርቶች ላይ የተመሠረተ ነው:: ማኅበራዊ አደረጃጀታቸውም የገዳ ሥርዓት ነው:: በአሁኑም ወቅት በቦረና የጉጂ÷ የኮንሶ÷ ሲዳማ÷ እና ደራሳ /ጌድዮ/ ሕዝቦች ዘንድ እንደሚኖሩ ይታመናል::

በአፍሮ ኤሽያቲክ የቋንቋ ቤተሰብ ሥር ከሚጠቀሱት ሁለተኛዎቹ አሞአውያን ሲሆኑ የአሞ /Omotic/ ተናጋሪ የሆኑና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የሚገኙ ናቸው:: መጀመሪያ የምዕራብ ኩሻውያን ቡድን በመባል ይታወቁ ነበር:: በጥራጥሬ እህል ምርት እና እንደ ድንችና ቀይ ሥር ያሉ በምድር ውስጥ የሚያፈሩ የምግብ እህሎች /tubers/ ላይ የተመሠረተ ኑሮን ይመሩ ነበር:: በመለኮታዊ እሳቤ ላይ የተመሠረተ የአንድ ሰው አገዛዝን /Divine Monarchy/ መሥርተዋል:: በዚህ የቋንቋ ቡድን ውስጥ እንደ ወላይትኛ፣ ጋሞኛ፣ ኩሎኛ፣ ጊምራኛ፣ ከፍኛ እና ኮምባትኛ ያሉቱ ቋንቋዎች ይገኙበታል:: የቋንቋዎቹ ተናጋሪ ሕዝቦችም በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ በከፋና በጋሞ ጐፋ ይገኛሉ::

ከአፍሮ ኤሽያቲክ የቋንቋ ቤተሰብ ሦስተኛዎቹ ሴማውያን ሲሆኑ ከሰሜን ዐረብ እንደመጡ ይታመናል:: እነርሱም በመልከዓ ምድራዊ



አሰፋፈር አንጻር በሁለት ተከፍለው ሰሜናውያንና የማዕከላዊ ኢትዮጵያ ሴማውያን በመባል ይታወቃሉ:: በአንድ ሰው አገዛዝ /Monoarchial System of Government/ ሥር በተለያዩ ስፍራዎች ማለትም በየሃ፣ ማታራ እና በትግሬ ምድር በኃውልቲ እንዲሁም በኤርትራ ይኖሩም ነበር:: የትግርኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች የዘሳን ከብት አርቢነትን እንዲሁም የግዕዝ ቋንቋ ተናጋሪዎች ግብርናንና ንግድን መተዳደሪያቸው አድርገዋል:: የፖለቲካና የባህል ዋና ማዕከል በማድረግም አክሱምን መሥርተዋል:: የደቡብ ኢትዮጵያ ሴማውያን በመባል የሚታወቁት:- አማራ፣ ጉራጌ፣ እና ሀረሪ ናቸው:: ጋፋትና አርጐባ የእነዚህ ቡድኖች ክፍል ናቸው::

ሌላውና በአንጋፋ የቋንቋ ቤተሰብነት የሚታወቀው ናይሎ-ሰሃራን (Nilo-Saharan) ተብሎ ይጠራል:: ይህ ደግሞ ከምዕራብ ሱዳን የመጡ ሱዳናውያንን የሚያካትት ሲሆን የበርታ፣ ኩናማ፣ ኮሞ፣ ጉሙዝ እና ሲይስ ቡድኖችን የሚያጠቃልል በብሉናይል ሸለቆ ሕዝብነት የሚታወቁ ናቸው:: እነርሱም ቅድመ ናይሎትስ /Pre-Nilotes/ በመባል ይታወቃሉ:: እነዚህ /Pre-Nilotes/ ወደ ኢትዮጵያ የመጡት በ3ኛው ሺህ ዓ.ዓ. ነበር::

የናይሎቲክ ባህላዊ የኑሮ ዘዴ በከብት ርባታና ስከብቶች እንዲሁም ለሰው ለምግብነት የሚያገለግሉ ጥራጥሬና መኖ /Millet/ ምርት ላይ የተመሠረተ ነው:: እነዚህ ሕዝቦች በአሁኑ ወቅት ኑወር እና አኝዋክ በመባል የሚጠሩ የኢትዮጵያን ሕዝብ የሚወክሉ ናቸው:: በናይሎ ሰሃራን አንጋፋ የቋንቋ ቤተሰብ ሥር የሚታወቁ ቋንቋዎች ደግሞ እንደ ቤጃኛ፣ ጉምዝኛ፣ ገሰብኛ፣ መአኛ፣ ኩናምኛ፣ ኑዌርኛ አኝዋክኛ ያሉቱ

ናቸው። የእነዚህ ቋንቋ ተናጋሪዎች በሰሜንና በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ናቸው።

ሰደተኞቹ ምዕራባዊ ሴማውያን ከደቡብ ዐረብ /የመን/ በ1000 ዓ.ዓ. የመጡ ናቸው። እነርሱም ሆሄያቶቻቸውን (የቃላት ፊደሎቻቸውን) በማምጣት በተለይ በጽሑፍ ቋንቋ በሰሜን ኩሻውያን ላይ ተጽዕኖ መፍጠር ችለዋል። ዐረቦች ለኢትዮጵያ "አቢሲንያ" የሚል ስያሜ የሰጧት ሲሆን ከየመን ወደ ኢትዮጵያ ከመጡ የሐበሻ ነገድ የተነሣ እንደሆነ ይነገራል። በአጠቃላይ ኢትዮጵያ ከ86 ቋንቋዎች በላይ ተናጋሪ ሕዝቦች እንዳሏት ይነገራል።

## 1.1.2. የኢትዮጵያውያን አምልኮ

### 1.1.2.1. አረማዊነት በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ ምድር ከክርስትና ብስራት አስቀድሞ የአረማዊነት መስፋፋት በከፍተኛ ደረጃ እንደነበረ ታሪክ ያመለክተናል። ወደ ኢትዮጵያ ምድር በመጀመሪያ እንደ ገቡ የሚነገርላቸው ከኖኅ ልጆች የካም ልጅ የሆነው የኩሽ ዘሮች እንደሆኑ ይነገራል። በዚህ በነገደ ኩሽ ትኩረት መሠረት ደግሞ በምድር ተንቀሳቃሽ የሆኑ ፍጥረታት ይመለኩ እንደ ነበረ የሚያመለክቱ የታሪክ ማስረጃዎች አሉ። እነዚህም የአምልኮ ሥርዓቶች ከፋርስ ወደ ኢትዮጵያ ሳይመጡ እንደማይቀሩ ይገመታል።

በኢትዮጵያ ምድር የእባብ (የዘንዶ) አምልኮ የተለመደ እንደ ነበረ የሥነ ቅርስ ባለ ሞያዎች በአክሱም ምድር ያገኟቸውን ማስረጃዎች ዋቢ በማድረግ ይጠቅሳሉ። በቤት እንስሳት፥ በአራዊት፥ በአእዋፍ፥ በኮረብታ፥



በሐይቅ፥ በወራጅ ውሀ፥ በሚሳቡ ፍጥረታት (የእባብ አይነቶች)፥ በዛፎች፥ በድንጋዮች የማምለክ ልምድ የነገደ ካም ዝርያዎች ትውፊት እንደ ነበር በኢትዮጵያ ቅድመ ክርስትና የነበረውን አምልኮ ታሪክ ይገልጽልናል።[2] እንደ አባ ጎርጎርዮስ አባባል:- «ለምሳሌ:- ለዘንዶ ይገብሩ፥ ዘንዶ ያመልኩ እንደ ነበር በኢትዮጵያ ታሪክ ነገሥት ተጽፏል። ይኸው የኢትዮጵያ ታሪከ ነገሥት እንደሚለው በኢትዮጵያ ሲመለክ የኖረውን ዘንዶ የገደለው የንግሥተ ሳባ አባት አንጋቦስ የተባለ ሰው ነው።»[3]

በሌላ አቅጣጫ የብዙ አማልክት አምልኮን ወይም መድብለ አማልክት (Polytheism) በቀይ ባሕር በኩል ወደ ኢትዮጵያ የገቡ ነጋዴች የተለያዩ የሰማይ፥ የምድርና የባሕር አማልክትን አስተዋውቀዋል። ከዚህም የተነሣ የፀሐይ፥ የጨረቃ፥ የከዋክብት አምልኮ ከነገደ ሴም ዝርያዎች ወደ ኢትዮጵያ የገቡ የሳባውያን ትውፊት (ውርስ) ነበረ የሚል ትረካ ይቀርባል። ይህም ዓይነት አምልኮ በደቡብ ዐረቢያ ከተገኘው የአምልኮት ቅርስ ጋር ስለሚመስስል ሳባውያን እንደ ሆሄያቶቻቸው (ፊደላቸው) ሁሉ ሥርዓተ አምልኮአቸውን ይዘው ገብተው ነበረ ቢባል ያስኬዳል። ይህ እንግዲህ እንደ ሥልጣኔ እንቅስቃሴ የተቈጠረና ሰዎች ከአበቧቸው ፍጥረታት ወደ ታላላቅ ግዑዛን ዓይኖቻቸውን በማቅናት ለአምልኮ የላቀ ነገርን መፈለጋቸውን አመላካች ነው።[4]

---

[2] *መሠረት ስብሐት ለአብ፥ ጮራ መጽሔት፥* "ክርስትና በኢትዮጵያ"ቁ.4ገጽ. 12
[3] አባ ጎርጎርዮስ፥ *የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፥* አዲስ አበባ፥ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፥ 1994፥ ገጽ 13
[4] *መሠረት ስብሐት ለአብ፥ጮራ መጽሔት፥*"ክርስትና በኢትዮጵያ"ቁ.4ገጽ.11

እንግዲህ የግሪክ አማልክት ቅድመ ክርስትና በኢትዮጵያ ምድር ይመለኩ ነበር:: የግሪክ አማልክት - ዙስ /Zeus/ ፤ የባሕር አምላክ በመባል የሚታወቀው ፖሲዶን /Poseidon/ እንዲሁም አሬስ /Ares/ ይገኙበታል:: የእባብ (የዘንዶ) አምልኮን የሚያካትት አረማዊነትም እስከ አሁን ድረስ ከቃልቻ ጋር በተያያዘ፥ በተለይ በኦሮሞ ሕዝብ ዘንድ እንዳለ ይታመናል:: ይህ አምልኮተ ጣዖት ከፋርስ ወደ ኢትዮጵያ መምጣቱም ይነገራል::

የደቡብ ዐረብ /Sabean/ አማልክት አልሞኳሽ /Almouquash or Elmouquah/ በኢትዮጵያ ይመለክ ነበር:: አሬስ /Ares/ ከክርስትና ብስራት በፊት የኢትዮጵያ ነገሥታት የግል አምላክ እንደ ነበር በቅርሶች ላይ በተደረጉ ጽሑፎች ተረጋግጧል:: በአጠቃላይ ዙስ Zeus/ የባሕር አምላክ እንደሆነ የሚነገርለት፤ ፖሲዶን /Poseidon/ እና አሬስ /Ares/ ምንጫቸው ከግሪክ እንደሆነና በኢትዮጵያ የአረማዊነት ታሪክ የተካተቱ እንደሆነ መረዳት ይቻላል:: ኢትዮጵያዊ የግዕዝ ስያሜ ለእነዚህ አማልክት እንደተጣቸውም በ300 ዓ.ም. በንጉሥ ኢዛና የተቀረጹ የቅርስ ጽሑፎች ያመለክታሉ:: ለእነዚህ የዐአረብ /Sabean/ እና የግሪክ አማልክት የግዕዝ ስያሜያቸውን በተመለከተም:- ማህረም- ለአሬስ/Ares/ ባህር-ለፖሲዶን፤ ለማይ ለዐረብ /Sabean/ አማልክት አልማኳሽ ማለትም ከ5ኛው ዓ.ም. በፊት በየሃ ይመለኩ ለነበሩ አማልክት ተሰጥተዋቸዋል:: በኃውልቲ - መላዞ ማለትም ለአክሱም ቅርብ በሆነ ስፍራም ለዚሁ ለአልማኳሽ የቆመ ቤተ መቅደስ እንደነበረና በአሁኑ ወቅት ግን ፍርስራሹ እንዳለ ይታመናል:: ንጉሥ ኢዛናም ከወርቅ፥ ከመዳብና ብር



የተሠራን የአሬስ 'Ares/ ሐውልት በሰሜኑ ግንባር የቤጃን /Beja/ ሕዝቦችን ድል አድርጐ እንደተመለሰ ያቆመው እንደነበር ይታመናል::[5]

### 1.1.2.2. የአንድ አምላክ /Monotheism/ አምልኮ በኢትዮጵያ

ቅድመ ክርስትና የአንድ አምላክ አምልኮ ታሪክ የጐላ ስፍራ ነበረው:: በ 1000 ዓ.ዓ. ንግሥተ ሳባ ወደ ኢየሩሳሌም ሄዳ ንጉሥ ሰሎሞንን መጐብኘቷና ከእርሱም ፀንሳ መምጣቷ፤ ከዚያም ቀዳማዊ ምኒሊክን መውለዷ የንግሥተ ሳባ ትውፊት ዘገባ እንደሆነ በሚነገርለት "በክብረ ነገሥት" ተጽፏል:: ክብረ ነገሥት በ1270 ዓ.ም. ምናልባት በአቡነ ተክለ ሃይማኖት ሳይጻፍ እንዳልቀረ ይነገራል:: ምክንያቱ ተክለ ሃይማኖት የእስራኤል ሊቀ ካህን የነበረው የሳዶቅ /Sadoc/ ዘር እንደሆኑ ስለራሳቸው ይናገራሉና ነው:: ምኒልክ ሲያድግ አባቱን ሠሎሞንን ለመጐብኘት ኢየሩሳሌም እንደሄደም ይተረካል:: ከዚያም ከሌዊ ነገድ ብዙ እስራኤላውያንንና የቃል ኪዳኑን ታቦት ይዞ ከመምጣቱ ጋር ተያያዞ ይሁዲነት በኢትዮጵያ የመስፋፋቱ ትውፊት ይተረካል::[6]

---

[5] Calvin Shenk, "Ethiopian Orthodox Christianity" in *Ethiopian Religion*, Nazreth: Bible Academy, 1970, p. 21

[6] Ibid.

### 1.2.3. እንማማር

ሐዋርያው ጳውሎስ ስለ ወንጌል ያልሆነው እንደሌለ በ1ኛው ቆሮንቶስ 9:19-23 አስረድቷል:: እንዲያውም በቁጥር 23 ላይ «በወንጌል ማኅበርተኛ እሆን ዘንድ ስለ ወንጌል ሁሉን አደርጋለሁ::» ይላል:: ሐዋርያው ጳውሉስ ስለ ወንጌል የሆነውን ስንመለከት የሆነው መሆን ትቶ ትምክህት የሚሆን ነገር የሌላቸውን አሕዛብን ለመጥቀም እነርሱን ሆኖ መገኘቱን እንመለከታለን (1ቆሮ. 9:19-23)::

ወንጌል አውዳዊ ሆኖ (በተጻፈበት ትክክለኛ መንፈስ) ሊሰበክ የተገባው መሆኑን የምንረዳው የቋንቋም ሆነ የባህል ርኩስም ሆነ ቅዱስ አለመኖሩንና እግዚአብሔርም በሰው ቋንቋ ለሰው ልጆች ራሱን መግለጡን ስናስተውል ነው:: ስለዚህም ምንም እንኳን መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈባቸው ቋንቋዎች የሰው ቋንቋዎች በመሆናቸው መለኮታዊ ቋንቋዎች ነበሩ እንደማንል ሁሉ የአይሁድንም ባህል ፍጹም ቅዱስ ባህል ብለን የሌላውን ሕዝብ ባህል በሙሉ ርኩስ ማለት አንችልም::

ሐዋርያው ጴጥሮስ የአይሁድን ባህል ቅዱስነት በማሰብ ለአሕዛብ ወንጌልን ላለማድረስ (ሐዋ. 11) እንዲሁም ከአሕዛብ ጋር በማዕድ ለመሳተፍ ማንገራገሩ በገላትያ መልዕክት ምዕራፍ 2 ላይ ከገላትያ አማኞች ጋር በማዕድ ሳለ ከያዕቆብ ዘንድ ሰዎች እንደ መጡ በሰማበት ወቅት በማፈግፈጉ ሐዋርያው ጳውሎስ ፊት ለፊት እንደተቃወመው እንገነዘባለን:: የአጠቃላይ የመጽሐፍ ቅዱስ እውነት የሚያስገነዝበንም አሕዛብ ክርስትናን ሲቀበሉ አስቀድመው አይሁድ መሆንም ሆነ ዕብራይስጥ እና ግሪክ ቋንቋ ማጥናት አልነበረባቸውም:: በራሳቸው ቋንቋና በራሳቸው ባህል ክርስቲያኖች እንዲሆኑ እውነቱን ማስተጋባት



ያሻል:: ከዚህም የተነሣ ወንጌል በባሕል ውስጥ ሊሰበክ ባሕል ግን በወንጌል ውስጥ መሰበክ እንደሌለበት አጽንዖት ሊሰጥበት ይገባል::

ስለዚህም አንድን ሕዝብ በተሳካና ያስመሰናክል ወደ ክርስትና እውነት ለማምጣት የሕዝቡን ማንነት ቋንቋና ባህል አስቀድሞ ማጥናት ወሳኝ ነው:: ከላይ ስለ ኢትዮጵያ ሕዝብ ማንነትና መልክዓ ምድራዊ አሰፋፈር ያለውም ገለጻ በዚህ ረገድ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ስለሚኖረው በተለይም በወንጌል መልዕክተኝነት በቤተክርስቲያን ተከላ የሚለማሩ አገልጋዮች ልብ ሊሉት ይገባል::

ለዚህ ከሕይወት ተሞክሮዬ ላካፍላችሁ:: በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ በወንጌል አገልግሎት የእረኝነት ተልእኮዬን በመወጣት ላይ ባለሁባት አንዲት አጥቢያ ቤተክርስቲያን ለአምልኮ ስንለባሰብ ብዙ ጊዜ የምንቸገርበት ነገር ቃለ እግዚአብሔር እየተሰበከ እንቅልፍ የሚወስዳቸው ሰዎች መብዛ ቸው ነበር:: እኔም በዚህ ጉዳይ ላይ ለፊ ጥናት አደረግሁ:: በኋላም ችግሩ በአዲስ አበባ ለረጅም ዓመታት ቢኖሩም የአማርኛ ቋንቋ የማያውቁና የባህል ግጭት ውስጥ የገቡ በርካታ የአንድ ብሔር ተወላጆች በአካባቢው መኖራቸውን ተረዳሁ:: ችግሩም እግዚአብሔርን ለማምለክ የሚችሉባቸው በቋንቋቸውና በባህላቸው የሚካሄዱ ፕሮግራሞች አለማግኘታቸው ነበር:: ለመፍትሔ አብረውኝ ከሚያገለግሉ ወገኖች ጋር በመመካከር በቋንቋቸውና በባህላቸው እግዚአብሔርን ማምለክ የሚችሉበት ሁኔታ ከተመቻቸላቸው በኋላ በአስደናቂ ፍጥነት ዕድገትና በንቃት በእግዚአብሔር ፊት መሆን መቻላቸውን መመልከት ችያለሁ::

በሌላ በኩል ደግሞ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ጥንታዊ ቋንቋ ግዕዝ በከፍተኛ ደረጃ ጥቅም ላይ ይውላል። የግዕዝ ቋንቋ ከአማርኛ የተሻለ ሥነ መለኮታዊ ፅንሰ ሐሳቦችን ይገልጻል ብል የተሳሳትሁ አይመስለኝም። ለዚህም በማስረጃነት የማቀርበው በአማርኛ ለመግለጥ አዳጋች የሆኑ በርካታ ሥነ መለኮታዊ ፅንሰ ሐሳቦችን ከግዕዝ መዋስ ለሥነ መለኮት ለምች አዲስ ባለመሆኑ ነው። ከዚህም የተነሣ ለግዕዝ ቋንቋ ከፍተኛ ክበሬታ አለኝ። ነገር ግን ከሰብከተ ወንጌልና ከቤተ ክርስቲያን ተከላ አንጻር ኢትዮጵያን በወንጌል ለመድረስ የግዕዝ ቋንቋን መጠቀሙ አቀበት መውጣት ይሆናል። በተለይ ደግሞ ኢትዮጵያ የብዙ ብሔሮች ሀገር እንደ መሆኗ ሕዝቦቿን አንድ የሚያደርጓቸው የጋራ ባህል ነጸብራቅ ቢኖራትም በዚያው መጠን በእያንዳንዱ ብሔር የባህል ልዩነት ሊኖር እንደሚችል መረዳት ያሻል። ስለዚህም ቋንቋውንና ባህሉን ያገናዘበ አገልግሎት ውጤታማነቱ አጠያያቂ አይደለም።

## 1.2. የክርስትና ብስራትና መስፋፋት በኢትዮጵያ

### **1.2.1. የክርስትና ብስራት በኢትዮጵያ**

ኢትዮጵያ ቅድመ ክርስትና የአረማዊነትና የአይሁድ እምነት ታሪክ የነበራት ሲሆን የክርስትናን ብስራት በተመለከተ አራት የተለያዩ አመለካከቶች ይሰነዘራሉ[7]:- የመጀመሪያው በሐዋ. 8:26-40 መሠረት በኢትዮጵያዊው ጃንደረባ በኩል የሚል ሲሆን ይህ ጃንደረባ ከፊልጶስ

[7] Sergaw Hable Selassie and Taddesse Tamrat, ***The Church of Ethiopia: A** Panorama of History and Spiritual Life*, 1971, p. 3



ወንጌልን ሰምቶ ክርስትናን ከተቀበለ በኋላ ተመልሶ ወደ ጥንታዊቷ ኢትዮጵያ በመምጣት እንደሰበከ ይነገራል።

ሁለተኛው በበዓለ ጰንጠቆስጤ ኢየሩሳሌም በተገኙ ኢትዮጵያውያን አማካኝነት ወንጌል ወደ ኢትዮጵያ እንደገባም የሚናገሩ አሉ። እንደ ጆን ክርሶስቶም ያሉ የታሪክ ተመራማርያን በሐዋ 2 መሠረት ለበዓሉ ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው የተመለሱ ኢትዮጵያውያን የሰሙትን የወንጌል የምሥራች ይዘው በመመለስ እንደ ሰበኩ ይናገራሉ። በዚህ ረገድ ደግሞ ወንጌል ከክርስቶስ ዕርገት በኋላ ለሠላሳ አመታት በአፍ የሚተላለፍ እንደ ነበርና በጽሑፍ እንዳልተዘጋጀ ያለው ታሪክ እነዚህ ኢትዮጵያውያን ወንጌልን በቃል እንጂ በጽሑፍ እንዳላመጡ አሳማኝነት ይኖረዋል።

ሦስተኛው ሐዋርያው ማቴዎስ ወንጌልን ለኢትዮጵያ እንዲያደርስ ዕጣ ወጥቶለት እንደ ነበርና እርሱም መጥቶ ስለ ወንጌል መሥዋዕት እንደ ሆነ የሚነገር ሲሆን የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ግን ወንጌልን ያለ ደም ማፍሰስ እንደተቀበለች ታምናለች። ከዚህም በተጨማሪ ማቴዎስ፣ በርተለሜዎስ ወይም ቶማስ ወንጌልን በአክሱም ሰብከዋል የሚል እምነትም አለ። የቅ/ ቶማስ እንደሆነ የሚነገርለት መቃብር በአዱሊስ እስከ ዛሬ እንዳለም ይነገራል። ሌላውና አራተኛው አመለካከት በቅ/ ፍሬምናጦስ በኩል ወንጌል ለኢትዮጵያ እንደተሰበከ የሚያመለክት ሲሆን ከዚያ በፊት ግን በኢትዮጵያ ምድር የሮም ነጋዴዎች የጸሎት ቤቶች እንደነበሯቸው፥ በግልም ያመልኩ እንደ ነበር ያስረዳል።

ስለ ቅዱስ ፍሬምናጦስ ያለው ትረካ እንደሚከተለው ነው:-[8] የጢሮስ ፈላስፋ እንደሆነ የሚነገርለት መሮጼዎስ ከሁለት ዘመዶቹ ከፍሬምናጦስና ከኤዲስዮስ ጋር ህንድን ለመጎብኘት በጉዞ ላይ እንዳለ ቀሰብ ያልቅባቸውና በአፍሪካ ወደብ ላይ ያርፋሉ:: ሕዝቡ በዚያን ወቅት ሰሮም ዜጎች ከፍተኛ ጥላቻ ስለነበራቸው በመርከቧ ውስጥ ያሉትን በሙሉ ገድለው ፍሬመናጦስንና ኤዲስዮስን ብቻ ያተርፏቸዋል:: በመቀጠልም ወደ ንጉሡ ኢላ-አሚዳ ያመጧቸዋል:: ኤዲስዮስን ጠጅ አሳላፊ፥ ፍሬምናጦስን ጃንደረባና ጸሓፊ አድርጎ እያገለገሉት ሳለ ንጉሡ ይሞታል::

ይህ ንጉሥ ኢላ-አሚዳ ከመሞቱ በፊት ወደ ሀገራቸው መሄድ ከፈለጉ እንዲሄዱ ፈቅዶላቸው ነበር:: ነገር ግን ንግሥቲቱ ልጇ ኢዛና እስኪያድግ ድረስ ሕዝብን በመምራት ረገድ እንዲያግዟት ለመኑቻቸው:: ልጇ አድጎ ሀገር ለመምራት በቻለበት ወቅት ወደ ሀገራቸው ለመሄድ ለመኑት:: ኤዲስዮስ ወደ ሀገሩ ሄደ:: ፍሬምናጦስ ግን ወደ እስክንድርያ በመሄድ ለአዲሱ ፓትርያርክ ለአትናቴዎስ ጉዳዩን ሁሉ ተርኮለት በአክሱም እያደገ ያለውን ክርስትናን የበለጠ ለማስፋፋት ጳጳስ እንዲሾም ጠየቀው:: ፓትርያርኩም የቀላውስቱን ጉባዔ ከሰበሰበ በኋላ ራሳቸውን ፍሬምናጦስ ለአክሱም ጳጳስ አድርጎ ሾማቸው::

ክርስትና የኢትዮጵያ ህገር አቀፍ ሃይማኖት ሆኖ በይፋ መገለጹ በሀገራችን ታሪክ ከፍተኛና የጎላ ድርሻ ነበረው:: ኢትዮጵያውያን ለቅዱስ ፍሬምናጦስ ያላቸው አቀባበልም ባወጡላቸው ስም የተንጸባረቀ ነበር::

---

[8] Jones, A.H.M. and Elizabeth Monroe, *A History of Ethiopia*, pp. 26-29



ቅ/ፍሬምናጦስን «አቡነ ሰላማ ከሳቴ ብርሃን» (የሰላም አባትና ብርሃንን ገላጭ) ብለው ስም አውጥተውላቸው ነበር:: በ356 ዓ/ም የአክሱም ገዢዎች የነበሩ ኢዛናና ሳይዘናስ ከተጠመቁ በኋላ ስማቸው አብርሃ (አብርሆት ሰጪ) እና አጽብሃ (ንጋት ሰጪ) መባላቸው እንመለከታለን:: ስለዚህም ክርስትና በኢትዮጵያ የጀመረው ከገዢ መደብ መሆኑን ታሪክ ያመለክተናል:: ይህን ደግሞ በሮም ምድር በነበረው የክርስትናን ብስራት ታሪክ ተቃራኒ የሚያደርገው በሮም የክርስትና ብስራት ከደሃው ማኅበረሰብ ሲጀምር በኢትዮጵያ ግን ከነገሥታቱ በመጀመሩ ነው::[9]

እዚህ ላይ በኢትዮጵያ የቅ/ ፍሬምናጦስን አስተዋጽኦ በዝርዝር ስንመለከት የተሰበከውን ወንጌል ተመርኩዞ የክርስትናን ትምህርት ማስተማራቸው ይነገራል:: ከዚህም በተጨማሪ እንደ አባ ጎርጎርዮስ አገላለጽ ቅ/ፍሬምናጦስ ሥርዓተ ቤተክርስቲያንን ማስጀመራቸው፥ ቅዱሳት መጻሕፍትን ወደ ግዕዝ ቋንቋ መመለሳቸው፥ የሳባውያን የፊደል አቀማመጥን ከግራ ወደቀኝ በመጻፍ ዘዴ ለውጦ የመጻፍና የማንበብ ዜዴ መፍጠራቸው፥ የኢትዮጵያውያንን ቋንቋና ባህል አውቀው ተልእኮአቸውን ለመወጣት መነሣታቸውና ከሳቸው አገልግሎት ዘመን ጀምሮ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን መንበረ ጵጵስናን ይዛ ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናት ጋር እንድትቆጠር ማድረጋቸው ተጠቃሽ ነው:: ቅ/ ፍሬምናጦስ ወደ ኢትዮጵያ ከመጡ በኋላ ክርስትናን ማስፋፋት እንዲችሉ ካደረጋቸው አንዱ የአገልግሎታቸው በተዓምራት የታጀበ መሆን ታላቅ ትኩረት ተሰጥቶታል::

---

[9] Calvin Shenk, "Ethiopian Orthodox Christianity" in *Ethiopian Religion*, Nazreth: Bible Academy, 1970, p. 1

## 1.2.2. የክርስትና መስፋፋት በኢትዮጵያ

### 1.2.2.1. ዘጠኙ ቅዱሳንና አስተዋጽዎአቸው::

ከ 350-650 ዓ/ም የክርስትና መስፋፋት በኢትዮጵያ እንዴት እንደ ነበር ስንመለከት:- ቅዱስ ፍሬምናጦስ በግብፃዊው ሚናስ እንደተተኩና ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የግብፅ (የእስክንድርያ) መሪነት በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ላይ እንደተንጸባረቀ እንመለከታለን:: እ.ኤ.አ. በ 480 ዓ/ም ወደ ኢትዮጵያ የመጡና በንጉሡ አቀባበል የተደረገላቸው ዘጠኙ ቅዱሳን ይባሉ እንደነበር ይታመናል::

ከዘጠኙ ቅዱሳን ውስጥ በጣም ታዋቂዎቹ:- ዘሚካኤል (አረጋዊ)÷ ጰንጠሌዎን÷ አፍጼ እና ገሪማ ወይም ይሳቅ ይባላሉ:: እነርሱም ከተለያዩ የዓስም ክፍሎች የመጡና የአንድ ዓይነት አስተምህሮት ተከታዮች ነበሩ:: ከዚህ የተለየ አስተምህሮታቸውም የተነሣ ከሀገራቸው ላይሰደዱ እንደማይቀር ይታመናል:: ስለዚህም ሁሉም የኬልቄዶን ጉባዔ ውሳኔን የሚቃወሙ እንደሆኑ ይነገራል::[12]

የዘጠኙ ቅዱሳን አገልግሎት የአራት ነገሥታት ማለትም የኢላ-አሚዳ (ዳግማዊ) /8 ዓመት/÷ ታዘና/12 ዓመት/÷ ካሌብ/30 ዓመት/ እና የገብረ መስቀል ንግሥና ዘመን በከፊል የሚያካትት እንደሆነ ይታመናል:: በአጠቃላይ የአገልግሎት ዘመናቸው ከ50 ዓመታት ያለፈ እንደሆነና በዚህ ረጅም የአገልግሎት ዘመን ከክርስትና መስፋፋት ባሻገር ለሥነ

[12] አባ ጎርጎሪዮስ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ ታሪክ ገጽ 22-23



ጽሑፍ እና አጠቃላይ የቤተክርስቲያን እንቅስቃሴ ታላቅ አስዋጽኦ አድርገዋል::[13]

ዘጠኙ ቅዱሳን በአክሱም የሕዝቡን ቋንቋ አጥንተው ከሕዝቡ ባህልም ጋር ራሳቸውን አስተዋውቀዋል:: በመቀጠልም ወደ ተለያየ ስፍራ በመሄድ ገዳማትን መመስረት ጀመሩ:: አባ ጰንጠሌዎንና አባ ሊቃኖስ ብቻ አክሱም አካባቢ ሲቀሩ ሌሎቹ ራቅ ያሉ ስፍራዎች ሄደው የባዕድ አምልኮ ያሰባቸውን ቦታዎች በወንጌል እንደደረሱ ታሪካቸው ያስረዳናል:: ዘሚካኤል (አረጋዊ) ወደ ደብረ ዳሞ በመሄድ የእባብ አምልኮን በማጥፋት ገዳም ተከሉ÷ አባ ጰንጠልዮን የአረማዊነት ቤተመቅደስን ወደ ቤተክርስቲያን ለወጡ÷ አባ አፍጼም ወደ የሃ በመጓዝ የሳባውያንን ማዕከልና ታዋቂውን ቤተመቅደስ ወደ ቤተክርስቲያን እንደ ለወጡ የታሪክ ምሁራን ሠርጋው ኃብለ ሥላሴና ታደሰ ታምራት በመጽሐፋቸው አስፍረዋል::[14]

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ለእነዚህ የወንጌል መልዕክተኞች የእረፍት ቀናቸውን በመዘከር መታሠቢያ ታደርግላቸዋለች::

[13] ዝኒ ከማሁ÷ ገጽ 23
[14] Serrgaw Hable Selassie and Taddesse Tamrat, The Church of Ethiopia: A Panaroma of History and Spiritual Life, pp. 7-8

### 1.2.3. እንማማር

የክርስትና ብስራት በኢትዮጵያ የነበረውን አንድምታ ስንመለከት በርካታ የምንማማርባቸው ነጥቦች እንዳሉ ግልጽ ነው፡፡ ክርስትና ለኢትዮጵያ የተበሰረባቸው መንገዶች እንደሆኑ ከተሰነዘሩት አራት ነጥቦች ውስጥ የመጀመሪያዎቹ ሦስቱን ስንቃኝ እያንዳንዳቸው ነጥቦች ያሏቸው የታሪክ መከራከሪያዎች የሚናቁ አይደሉም፡፡ በእኔ እምነት አራተኛውና በቅዱስ ፍሬምናጦስ በኩል ክርስትና ለኢትዮጵያ እንደተበሰረ የሚያመለክተው ታሪክ ጉልህ ስፍራ ሊሰጠው የቻለው ኢትዮጵያ ከእስክንድርያ ቤተ ክርስቲያን ጋር ካላት ትስስርና በፖሰቲካ ጦስ ቤተ ክርስቲያን ለሁለት ከመከፈሏ አንጻርና እናት ቤተክርስቲያንን ለማመልከት ካለው ታሪክ እንጂ ወንጌል ለኢትዮጵያ የተበሰረው በቅዱስ ፍሬምናጦስ ነው የሚለው መከራከሪያ ተጨባጭ አይመስለኝም፡፡ ይህንን በል ቅ/ ፍሬምናጦስ ለኢትዮጵያ ያበረከቱትን ጉልህ አስተዋጽኦ ለመካድ እንዳይደለ ሊሰመርበት ይገባል፡፡ በስዚህም ከቅ/ ፍሬምናጦስ በፊት በኢትዮጵያ ወንጌል ሊሰበክ መቻሉ ተአማኒነት ሊኖረው የሚችል ቢሆንም ቤተክርስቲያናዊ አደረጃጀት እና ሥርዓተ ቤተክርስቲያን መጀመርን በተመለከተ ያለው የታሪክ ማስረጃ ከቅ/ ፍሬምናጦስ ጋር የተያያዘ በመሆኑ ተያይዞ ሊነገር ይችላል፡፡

ወደ ቅ/ ፍሬምናጦስ አስተዋጽኦ ልመለስና ከታሪክ እንደምንማረው ክርስትና በገዢ መደብ ላይ ተጽእኖ ማምጣት መቻሉ በፍጥነት ብዙዎችን ለመውረስ ያለው አስተዋጽኦ ቀላል አይደለም፡፡ በቅ/ ፍሬምናጦስ በኩል ለአክሱም ገዢዎች ወንጌል መድረሱ ለክርስትና መስፋፋት ካለው አስተዋጽኦ በዚህ ዘመን ያለን የወንጌል መልዕክተኞችም ትምህርት በመውሰድ ንጉሡን ወንጌል ለባለሥልጣናት



የማድረስን ጉልህ ጠቀሜታ ልናስተውል ያሻል፡፡ ከተልእኮአችንም አንጻር ወንጌልን ለምስኪኑና በኑሮው ጉስቁልና ረዳት ለሚሻው ብቻ ሳይሆን «እግዚአብሔር ማን ነው?» እስኪል በሥልጣኑ ለሚመካውም ማድረስ እንዳለብን መዘንጋት የለብንም፡፡ ይህ ደግሞ ከታች ወደ ላይ መውጣት ያለውን አዳጋችነት በማቃለል ከላይ ወደታች በመውረድ ረገድ በፍጥነት ወንጌልን የማዳረስ ተልእኮን ስመወጣት ያስችላል፡፡ ለዚህም በምሳሌነት በቅርብ ጊዜ ትዝታችን በከተማችን በአዲስ አበባ ሹማምንት የሃይማኖት ቆባቸውን እንዳልጣሉ ያስመሰከሩባቸው ድርጊቶቻቸውና ውጤቱ ከማስተዋል ልንማር ይገባል፡፡

ቅዱስ ፍሬምናጦስ በሥብከተ ወንጌል ረገድ ያከናወኑት ሌላው ጉልህ አስተዋጽኦ መጻሕፍትን ወደ ግዕዝ ቋንቋ ስመመለስ ያደረጉት ጥረት ነው፡፡ ምናልባትም በጊዜው የእስክንድርያ ቋንቋ በነበረው በዐረብኛ ስመስበክና ሕዝቡም ሁሉ ዐረብኛ እንዲማር አድርገው ቢሆን ኖሮ፤ ለትርጉም ሥራ የሚውሰው ድካም እንደሚቀንስ ቢታሰብም ወንጌል ተቀባይነት የማግኘቱም ሆነ ባዕድነት ሳይሰማው በኃይል የመሮጡን ጉዳይ አጠያያቂ ያደርገው ነበር ማስት ያስችለናል፡፡ ይህም ደግሞ የቅዱሳን ቋንቋዎች መዛግብትን ስማስፋፋት ካልሆነ በቀር አስተርዮተ እግዚአብሔር በቋንቋ መረጣ እንዳልተስተናገደ ያለውን እውነታ የሚከድ ይሆናል፡፡

በሌላ በኩል ደግሞ የቅ/ ፍሬምናጦስ አገልግሎት በተአምራት የታጀበ መሆኑ ከሀገራችን ታሪክ አንጻር የነበረው የልዩ ልዩን የአማልክት አምልኮ በመገዳደር፤ የእግዚአብሔርን ኃይል ታላቅነት በማንጸባረቅ እግዚአብሔር በሌሎች አማልክት ላይም አምላክ መሆኑን በማስመስከር

ረገድ የጎላ አስተዋጽኦ ይኖረዋል:: በዚህ ረገድ መስተዋል የሚገባው ነገር ቢኖር ባለ ገድሉ ራሱ እግዚአብሔር ብቻ መሆኑን ነው::

በክርስትና መስፋፋትም ረገድ ዘጠኙ ቅዱሳን ያበረከቱት አስተዋጽኦ ለትምህርታችን የሚሆኑ በርካታ ነጥቦችን የያዘ ነው:: እንደ ቅ/ ፍሬምናጦስ በወቅቱ የአክሱም ቋንቋ የሆነውን ግዕዝን በማጥናት፥ የተለያዩ አማልክት ይመለኩባቸው በነበሩበት ስፍራዎች ላይ በማተኮርና የእግዚአብሔርን ኃይል በመግለጥ በአምልኮተ ጣዖት መቅደሶች ምትክ ቤተክርስቲያንን በመመሥረት ያደረጉት አስተዋጽኦ ልብ ልንለው የተገባው ነው:: ቤተ ጣዖታትን ከመቀየር ድርጊታቸው የምንረዳው ደግሞ ሕዝቡ ወደ ቀድሞ አማልክቶቹ ለመመለስ እንዳያስብ ከማድረጉም በላይ የአምልኮተ ባዕድ መታሠቢያውን የማሳጣት አስፈላጊነትን ነው::

ለክርስትና እውነት መዳበር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸውን መንፈሳዊ ቃላትንም በተመለከተ፤ እስከ ዛሬም ድረስ በአማርኛ ቋንቋ ለምንጠቀምባቸው የሥነ መለኮት ቃላት መዳበር ተጠቃሽ ናቸው:: ከዚህም በተጨማሪ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ ግዕዝ ለመመለስ የከፈሉትም መስዋዕትነት የላቀ ነው:: ከዚህ የዘጠኙ ቅዱሳን ታሪክ የምንማረው ትልቁ ነገር፣ በቅዱሳት መጻሕፍት መተርጎምና ቤተክርስቲያን መንፈሳዊውን ትምህርት ለሰዎች ለማዳረስ በምታደርገው ጥረት ዛሬ ድረስ እየተጠቀመች ያለችው፤ እግዚአብሔር በዘጠኙ ቅዱሳን አማካኝነት ቃሉ ለምድራችን እንዲደርስ በማድረጉ ነው:: በመሆኑም በመጻሕፍትና በመንፈሳዊው ትምህርት ረገድ የሚደረግ ትጋት ለትውልድ የሚተርፍ በመሆኑ አርዓያነታቸውን የመከተል አስፈላጊነት ልብ ልንል ይገባል::



በሌላ በኩል ደግሞ ዘጠኙ ቅዱሳን ኢትዮጵያን እንደተወለዱባት አገር ቆጥረው አገልግሎታቸውን መወጣታቸው የሚያመለክተው፤ እንደ እግዚአብሔር አገልጋይ አለቃቸው ራሱ እግዚአብሔር መሆኑን ከልብ የተረዱ በመሆናቸው ነው:: በመሆኑም እኛም በአገልግሎታችን ከፍተኛ ትኩረት ልንሰጠው የሚገባው ነገር የእግዚአብሔርን እልቅና ተመልክተን ባዕድ በምንለው አገር ሳይቀር በወንጌል አገልግሎት ትጋትን እንድንጨምር ያበረታታናል:: ከዚህ በተጨማሪ የቤተክርስቲያን ተከላ ስልታቸው በተለይ በዋና ከተማይቱ በአክሱም ላይ ብቻ ከማተኮር ወደ ተለያዩ ስፋራዎች ተበታትነው ማገልገላቸው ለአግልግሎቱ ልባሞች መሆናቸውን አመላካች ነው::

## 1.3. ድኅረ ክርስትና:- የወንጌል ሩጫና ተግዳሮቶች በኢትዮጵያ

### 1.3.1. መንግሥትና ክርስትና በኢትዮጵያ

የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ከዐፄ ካሌብና ከልጃቸው ከገብረ መስቀል በኋላ በእስክንድርያ ሳይሆን በቢዛንታይንና በሞኖፋይዛይት ማለትም በደቡብ ዐረብያ ተጽእኖ ውስጥ ወድቃ ስለነበር ማሽቆልቆል እንደ ጀመረች ይነገራል:: በተለይም ደግሞ ከእስልምናና ከዐረቦች ተጽዕኖ የተነሣም አረማዊነት እየጎለበተ በመሄዱ ኢትዮጵያ ከሌሎች አብያተ ክርስቲያናትም ተለይታ እንደነበርም ይወሳል:: ከዚህም የተነሣ ከግብፅ፣ ከመካከለኛው ምሥራቅ፣ ከዐረብና ከኑብያ ተራራቀች:: ስለዚህም ኢትዮጵያ በምሥራቅ ከእስልምና በደቡብ ከአረማዊነት የተጎሩበተች የክርስቲያን ደሴት ሆነች፤ የአይሁድ እምነትም እያደገ ሄደ:: ከ10ኛው እስከ 13ኛው ክፍለ ዘመን ስለቤተክርስቲያኒቱ የሚታወቀው ነገር ጥቂት ነው:: ለዚህ ደግሞ በዋናነት የሚጠቀሰው በ10ኛው ክፍለ ዘመን

ዮዲት/ጉዲት/ የአክሱምን መንግሥት ያዘችና የአቢሲንያ ንግሥት በመሆን ለ40 ዓመታት በነበራት የንግሥና ዘመን በአክሱምና በክርስትና ላይ ከፍተኛ ውድመትን ማስከተሏ ነው::[19]

ኢትዮጵያ በ12ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ክርስትና ተስፋፍቶ በተለይ በአዲስ የክርስቲያን የንግሥና ሐረግ በዛግዌ ሥርወ መንግሥት ትተዳደር በነበረበት ወቅት በታዋቂው ንጉሥ በንጉሥ ላሊበላ እስከ ዛሬም ድረስ በታሪክ ቅርስነት በስሙ የሚጠራ ከአንድ ድንጋይ ተጠርቦ የተሠራ ቤተክርስቲያን ይገኛል:: እንደ አባ ጎርጎርዮስ አገላለጽ ስለ ንጉሥ ላሊበላ ከሚነገሩት ውስጥ:- «በሺህ 189 ዓ/ም ላላህ አዲን በሦስተኛው የመስቀል ጦርነት ኢየሩሳሌምን በያዘ ጊዜ ከክርስቲያን ቅርሶች ዋናዎቹን በጎልጎታ በሚገኘው በቅዱስ መቃብር አጠገብ ያለውን ንግሥት ዕሌኒ ቅዱስ መስቀሉን ያስወጣችበትን ዋሻና በቤተልሔም ጌታ የተወለደበትን ጎል ለቅዱስ ላሊበላ በስጦታ ያበረከተው መሆኑን ጽፏል:: የላሊበላን ዘመነ መንግሥት የኢትዮጵያ ቤተክርስትያን ታሪክ የሚታወስበት ሌላው ምክንያት ደግሞ ጻድቁ ንጉሥ በከተማው የሠራቸው ቦሥራ አንዱ አብያተ ክርስቲያናት ናቸው::»[20]

የዛግዌ ሥርወ መንግሥት ያበቃው በ1270 ዓ.ም ቅ/ተክለ ሃይማኖት/ ኢትዮጵያዊ መነኩሴ/ የንጉሥ ሰሎሞንን የንግሥና ሐረግ በንጉሥ ይኩኖ አምላክ አማካኝነት እንዲቀጥል ባደረጉበት ወቅት ነው:: የዚህ የሰሎሞናዊ ሥርወ መንግሥት እንደገና መነሣት ለቤተክርስቲያንና

---

[19] አባ ጎርጎርዮስ÷የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤ/ክ ታሪክ÷ገጽ 30
[20] ዝኒ ከማሁ÷ ገጽ 39



ለመንግሥት አንድ መሆን በምክንያትነት ይጠቀሳል:: በመቀጠልም የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን እንደገና ከእስክንድርያ ቤተክርስትያን ጋር አንድነት በመፍጠር የስፊ መሬት ባለቤት ሆነች:: እንደ ፍትሐ ነገሥት አገላለጽ አቡኑ በዜግነት ኢትዮጵያዊ መሆን አይችልም:: በርካታ መነኮሳትም ከግብፅ መጥተው ተሐድሶ የሚያሻትን ቤተክርስቲያን እንደገና ለማነቃቃት ጥረት አድርገዋል:: ቅዱሳት መጻሕፍትን ተርጉመዋል:: በዚህ ዘመን ታላቅ ንጉሥ እንደሆነ የሚነገርለት ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብም የቅዱሳት መጻሕፍት መጻፍንና የቤተክርስቲያን ሕንፃ መታነጽን በብርቱ ደግፏል! የስንበት ክብረ-በዓላትን አጠናክሯል ሕዝቡንም በማስተማር ላይ ከፍተኛ ትኩረት አድርጓል::

በ18 እና በ19ኛው ክፍለ ዘመን በዘመነ መሳፍንት ከኢትዮጵያ ሕዝብ ይልቅ ቤተክርስቲያን አንድነትን ተቀዳጀች:: ይሁንና አስቀድሞ ተነሥቶ በነበረው በክርስቶስ ልደት ዙሪያ እንደገና ክፍፍል ሆነ:: ይህ ደግሞ በጎንደር (ሦስት ልደት) እና በትግሬ (ሁለት ልደት) መካከል ችግርን አስከተለ:: (ለዚህ የሥነ መለኮት ጭብጥ ተጨማሪ ግንዛቤን ለማግኘት:- *እኔን ማን ትሉኛላችሁ?* የሚለውን መጽሐፍ መመልከት ይቻላል::)

በ19ኛው ክፍለ ዘመን መግቢያ ላይ ለተወሰነ ጊዜ ኢትዮጵያ ያለ ጳጳስ ነበረች:: በዘመነ መሳፍንት ማብቂያ ላይ ዐፄ ቴዎድሮስ በሃይማኖታዊ ቅንዓት ተነሱ:: ድርብ ጋብቻን በመቃወምና ሙስሊሞችን ወደ ክርስትና ለማምጣት በሚያበረታታ መንገድ የክርስትናን እምነት ለማደለ ሞከሩ:: በቤተክርስቲያን መሬትና ሀብትም ላይ የመቆጣጠሪያ መረብን ዘርግተው ለመንግሥት ድጋፍ ለማስገኘት ጥቅም አዋሉት:: ለአንዲት ቤተክርስቲያን ሁለት ቀሳውስትና ሦስት ዲያቆናትን ብቻ መመገብ የሚያስችላትን መሬት እንዲኖራት አደረጉ:: የተቀረውን መሬት ግብር

መከፈል ለሚችሉ ገበሬዎች ሰጡ:: የተቀሩት ካህናት እንደማንኛውም ሰው ግብር ገብረው መኖር እንዲችሉ መሬት ተሰጣቸው:: ይህ የተሐድሶ ሙከራቸው ካሕናትን በጠላትነት አስነሣባቸው::[21]

በዐፄ ቴዎድሮስና በግብፃዊው ጳጳስ በአቡነ ሰላማ መካከል የነበረው ግንኙነትም ከጊዜ ወደ ጊዜ እየከፋ ሄደ:: በቤተክርስቲያን ንብረትና የገቢ ምንጭ ዙሪያ ውዝግብ መነሣት ቀጠለ:: ጳጳሱ ግብፃዊ በመሆናቸው ውጥረት እየነገሠባቸውና እየተረበሹ መጡ:: ዐፄ ቴዎድሮስ የተሐድሶ እርምጃቸውን እየገፉበት በሄዱና ከዕቅዳቸው ለመመለስ ባልፈቀዱ ቁጥር ከአቡነ ሰላማና ከካህናቱ ጋር የነበረው ግንኙነት እየሻከረ ሄዶ አቡነ ሰላማን መቅደላ ላይ ታሰሩ፤ በ1860 ዓ.ም እዚያው በእስር ላይ እንዳሉ ሞቱ:: ዐፄ ቴዎድሮስ በ1857 ጎንደርን በመበዝበዝ በእሳት አጋይተዋት አጥፍተዋት እንደነበር ይነገራል:: በዚህም የጎንደር አብያተ ክርስቲያናት በሙሉ በእሳት እንደተቃጠሉና ጠቃሚ የተባሉ ነገሮችንም በሙሉ ንጉሡ ለራሳቸው እንዳጋዙም ይወሳል:: ከካህናት ጋር የነበረው መጥፎ ግንኙነት ንጉሡን የገንዘብ ድጋፉ ከማሳጣቱም በላይ ሕዝብ እንዲነሣባቸው አድርጓል:: ቤተክርስቲያን በግልም ሆነ በአገር ዓቀፍ ደረጃ የአንድነት ዋና አጋፋሪ ነበረች:: ዐፄ ቴዎድሮስ ከአብያተ ክርስትያናት ጋር ራሳቸውን አስማወዳጀታቸው ኢትዮጵያን አንድ አድርጎ ለመግዛት አላስቻላቸውም ነበር::[22]

[21] Bahru Zewde: *A History of Modern Ethiopia*: 1855-1974, Addis Ababa, University Press, 1991, p. 35

[22] Ibid, p. 36



በመቀጠልም ዮሐንስ አራተኛ በሃይማኖት ዙሪያ አንድነትን ለማምጣት ጉጉት ነበራቸው:: በ1870 የተደረገው ጉባኤ በቤተክርስቲያን የነበሩ የአስተምህሮት ውዝግቦችንና ሚስዮናውያንን ለማረም ነበር:: ከዚህ በተጨማሪ እስላሞች በሦስት ዓመታት፥ አረማውያን ደግሞ በአምስት አመታት ውስጥ ክርስትናን እንዲቀበሉ ትዕዛዝ አወጡ:: ይህ መመሪያ ሙሉ ለሙሉ ተፈጻሚነት ባያገኝም የኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን በአንዳንድ አከባቢ አማኞችን በማግኘት ጠንከራ ደረጃ ላይ መድረስ ቻለች::[23]

ዳግማዊ ምንሊክ ግዛ ቸውን ባስፋፉባቸው አዳዲስ ስፍራዎችም ቤተክርስቲያኒቱ በርካታ አባላትን ማግኘት ቻለች:: የአማርኛን ቋንቋ፥ ባህልና የኦርቶዶክስ ክርስቲያን በተቆጣጠሯቸው ስፍራዎች በምዕራብ፥ በምሥራቅና በደቡብ የማስተዋወቅ ተልዕኮ ነበራቸው:: ሌላው የቤተክርስትያን ተግዳሮት በልጅ እያሱ ዘመነ መንግሥት (በይፋ እስልምናን በተቀበለና ራሱን ከዙፋን ባገለለ ንጉሥ ዘመን) ነው:: ይህ እስከ ጣልያን ወረራ ድረስ በቤተ ክርስትያን ላይ የመጨረሻው ተግዳሮት ነበር::[24]

በዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት የቤተ ክርስቲያን ታሪክ የሃይማኖት ነጻነትን በተመለከተ በ1931 ዓ/ም ሕገ መንግሥት ላይ መካተቱ ተጠቃሽ ቢሆንም አተገባበርን በተመለከተ ግን ከፍተኛ ችግር ተስተውሎበታል:: ከማውቃቸው አንድ አረጋዊ ለመረዳት እንደ

[23] አባ ጎርጎርዮስ፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፥ ገጽ
[24] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ

ቻልኩትም የአርዮሳውያን ትምህርት በኢትዮጵያ በፍራ ማግኘት የጀመረውም በዐፄ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት ነበር:: እንደ እኚህ አረጋዊ አገላለጽ የጊዮርጊስ እለት ለንግሥ ዐፄ ኃይለ ሥላሴም በተገኙበት አንድ ባህታዊ:- «ዐፄ ኃይለ ሥላሴ:- ወልድ ፍጡር ነው ለሚሉ አርዮሳውያን በዚህ በአዲስ አበባ ከተማ ለያውም በአውራው መንገድ በቸርቸር ጎዳና ቢሮ እንዲከፍቱ አድርገዋል!» በማለት በሕዝብ ፊት ቢያሳጧቸው በፍጥነት ከሕዝቡ መካከል ወጥተው የአርዮሳውያን ቢሮ እንዲዘጋ ማዘዛቸውን መረዳት ችያለሁ::

በ1929 ፋሺስት ሙሶሎኒ ኢትዮጵያን ከፋፍሎ ለመግዛት ባደረገው ጥረትም ቫቲካን ከጎኑ ተሰልፋ እንደነበር ይነገራል:: ይህ ደግሞ የዓለም ክርስቲያኖችን ያጠያየቀ ነገር ነበር::

በአጠቃላይ መንግሥትና ቤተ ክርስቲያን በኢትዮጵያ ያላቸው ቁርኝት አንዱ በሌላው ለመጠቀም ባለው ሐሳብ በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ ሲሆን መሐመዳውያን በርካታ ጎረቤት አገሮችን በትምህርታቸው ሲያጥለቀልቁ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያንም «የክርስቲያን ደሴት» የሚል ስያሜን ለሀገራችን ማስጠቷን ታሪክ ያመለክተናል::

### 1.3.2. የ«ቅዱሳን» ገድልና የወንጌል ተግዳሮት በኢትዮጵያ

በኢትዮጵያ ከፍተኛ ክብር የሚሰጣቸውና ተጋድሎአቸው ትኩረት ተችሮት በቅዱሳት ስፍራ የተቀመጡ በርካታ ሰዎች አሉ:: እያንዳንዱ አብያተ ክርስትያናት ስለ ቅዱሳን በክብረ-በዓላት ቀኖቻቸው የሚነበቡ



በንክላር አሏቸው:: ካልቪን ሸንክ *Ethiopian Religion* በተባለው መጽሐፋቸው በኢትዮጵያ የቅዱሳንን ሕይወት ከታሪክ አንጻር እንደሚከተለው ተከፋፍሏል[25]:-

በአክሱም ዘመን:- ዘጠኙ ቅዱሳን:- አረጋዊ (ከዘጠኙ አጅግ ታዋቂው)፥ያሬድ (የቤተ ክርስቲያን ዜማ ደራሲ)፥ ንጉሥ ካሌብ (በ6ኛው መቶ ዓ.ም የደቡብ ዐረብን የታደገ ጀግና)! አባ ጎርጎርዮስ እንደሚሉት ከሆነ ደግሞ እኚህ ንጉሥ:- «በክርስቲያኖች ላይ በሀገረ ናግራን የተነሣውን ዕልቂት ለማስወገድ ዘምተው ክርስቲያኖችን ነፃ ያወጡና በምንኩስናም ሕይወት የአበውን አሠረ ጽድቅ ፈጽመው ያረፉ ደገኛ ጻድቅ ንጉሥ ስለ ነበሩ ዐፄ ካሌብ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቁጥራቸው ከጻድቃን ነው::»[26]

በመሸጋገሪያ ዘመን:- ላሊበላና ነዓኩቶ ለአብ (ሁለት የዛግዌ ሥረወ መንግሥታት) እንዲሁም ቅ/ ተክለ ኃይማኖት::

በስደት ዘመን:- በሰላታ ሚካኤል፥ የደብረ ሊባኖስ ገዳም ፊልጶስ፥ ተዓምራት አድራጊው አሮን ፥ የደብረ ቢዘኑ ፊልጶስና ንጉሥ ቴዎድሮስ::

[25] Calvin Shenk, "Orthodox Christianity" in Ethiopian Religion, p.

[26] አባ ጎርጎርዮስ፥ *የኢትዮጵያ ኦ. ተ. ቤተ ክርስቲያን ታሪክ፥* ገጽ 27

**በዘርዓ ያዕቆብ ዘመን (1434 - 1468)፡-** ንጉሥ ዘርዓ ያዕቆብ፥ ባስቤቱና ጀነራሉ እምደ ሚካኤል ቅዱሳን ናቸው። አፄ ዘርዓ ያዕቆብ የቤተክርስቲያንን ሥነ ጽሑፍና ኪነ ጥበብ ያስፋፋ፤ አምልኮተ ጣዖትን ከኢትዮጵያ ለማጥፋት ከፍተኛ ተጋድሎ ያደረጉ ከ 1434- 1468 ዓ/ም የነገሡ እንደነበር ይታመናል። ከእኒህ ንጉሥ ጋር በተያያዘ ያለው የጻቅነት ትረካ እንደሚከተለው ቀርቧል፡- "ዜና መዋዕላቸው እንደሚለው ደቂቀ እስጢፋኖስ የሚባሉ ለእመቤታችንና ለቅዱስ መስቀል ስግደት አይገባም የሚሉ መናፍቃን እንደ ተነሡ ይጽፋል።

ይኸው ዜና መዋዕል እንደሚለው እነዚህን መናፍቃን እንዲበቀሉ የተሰበሰቡትን ምእመናን ጠየቁ። ሁሉም በሞት ቅጣት እንዲቀጡ በየነባቸው። በመጨረሻም አፍንጫቸውን ተፎንነው ምላሳቸውን ተቆርጠው፤ በደንጊያ ተወግረው የካቲት ሁለት ቀን ሞቱ፤ በ38ኛው ቀን መጋቢት 10 ቀን የመስቀል ዕለት በዚያ ቦታ ብርሃን ወርዶ ታየ። ስለዚህም ይህችን ቦታ ደብረ ብርሃን ብለው ለየሟት። ይህ ቦታ በሸዋ ክፍለ ሀገር በተጉለትና ቡልጋ አውራጃ የሚገኘው ደብረ ብርሃን ሥላሴ ሳይሆን አይቀርም። ድርጊቱ የተፈጸመው (በ1424 - 1460) ገደማ ነው።"[27] ቤተ ክርስትያኒቱ የዐፄ ዘርዓ ያዕቆብን አማላጅነት የምታምንበት መሠረት በዚህ በሰው ዘር ላይ በተፈጸመ ዘግናኝ ድርጊት ላይ ነው።

**የፖርቹጋሎች ዘመን፡-** እምነታቸውን ከጥቃት ለመከላከል ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያላቸው ልብነ ድንግልና ገላውዴዎስ ቅዱሳን ናቸው። የሴት

---

[27] ዝኒ ከማሁ



መነኮሳት (nuns) የምንኩስና ሥርዓት መሥራች ወለተ ጴጥሮስ በዚሁ ዘመን ከሚጠቀሱ ቅዱሳን አንዷ ናቸው።

ስለ እያንዳንዱ ቅዱሳን የሚባለውንና ያለውን እምነት መረዳት ያሻል። ስለ ቅዱሳን ስናነሳ ከሁሉ የላቀ ስፍራ የሚሰጣት የጌታችን እናት ቅድስት ማርያም ናት። ስለ ቅድስት ማርያም ያለው የቅድስና መሠረት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ አንድ ላይ ያለውን ክፍል ተስታኮ የእርሷን ብፅዕናና ቅድስና በመንተራስ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ በቶአምረ ማርያም ላይ የተጻፉና በመጽሐፍ ቅዱስ ያልተደገፉ ትውፊቶች ላይ የተመሠረተ ነው። በጻድቃንነት ከሚታወቁቱ በዋና ዋናዎቹ ላይ ያለው ትምህርት እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

### ሀ. ቅድስት ማርያም

ስለ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እናት ስለ ቅድስት ማርያም ውልደት፥ የልጅነት ዘመኗ ከልጇ ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ ጋር ያሳለፈችውን በተለይም ከስቅለቱ ጋር የተያያዘና በወንጌላት ከተጠቀሱ ውጪ፤ በርካታ መጻሕፍት በቀደምት የክርስትና ዓለም በመካከለኛው ምሥራቅ በስፋት ይታዩ እንደነበር ታሪክ ያመለክታል። ስለ ማርያም በዕብራይስጥ፥ በሲርያና በዐረብኛ እንዲሁም በግዕዝ ቋንቋዎች የተጻፉ በርካታ ትረካዎች ነበሩ። ከእነዚህም ውስጥ በርካታ ትርጉሞችና በተመሳሳይ ርዕስ በግዕዝ ብቻ ተጽፈው የሚገኙ ወጥ ሥራዎችም ይገኙባቸዋል። ብዙ የአገልግሎት መጻሕፍት፥ ጸሎትና .መዝሙራት የእርሷን ድንግልናና አማላጅነት የሚያመለክቱ ናቸው።

ስለ ማርያም ድንግልናም ያላቸው እምነት:- "... በድንግልና ሳለች ከእርሷ ተወስደ ድንግል ማርያምን እናቴ አላት ከተፈጠረች ጀምሮ በምንም በምን ከድንግልናዋ አልተለወጠችም::"[28] በጣም ከሚጠቀሙባቸው መጻሕፍት ውስጥ የሃና ታሪክ÷ ውዳሴ ማርያም÷ አስተርእዮ ማርያም በዮሐንስ ወልደ ዘብዴዎስ÷ አርጋኖን ውዳሴዋና የማርያም ኪዳን ይገኙበታል:: ቤተ ክርስቲያኒቱ እነዚህንና ሌሎችም ስለ ማርያም በርካታ ትውፊቶች ትቀበላለች::

የኦርቶዶክስ ሊቃውንት ስለ ማርያም ከኃጢአት አንጻር ባላቸው ትምህርት ወጥነት የላቸውም:: አንዳንዶች ጥንተ አብሶ እንዳለባት÷ ነገር ግን በራሷ አስተሳሰብ÷ በአንደበትና በግብርም ያለ ኃጢአት እንደሆነች ሲናገሩ ሌሎች ደግሞ ጥንተ አብሶ ያለባት መሆኑን አይቀበሉም::[29] እርሷ በመንፈስ ቅዱስ በተለየ ሁኔታ "የአምላክ እናት" እንድትሆን መዘጋጀቷን ያምናሉ:: በስሟ ጾምን በማወጅ ከነሐሴ 1-16 ያለውን ጊዜ ያከብራሉ:: በርካታ አብያተ ክርስቲያናት በስሟ በመሰየም በርካታ ቀናትን ለመታሠቢያነት አድርገውላታል:: ድንግል ማርያም ከፍጡራን በላይ÷ ከፈጣሪ በታች ክብሯ ከፍ ያለ ስለሆነ የአክብሮት (የጸጋ) ስግደት እንደሚገባት ይናገራሉ::[30] የቅድስት ማርያም ሕይወት ከእግዚአብሔር

[28] ሃይ አበ. ም 53 ክ 1 ቁ 22

[29] ሠይፈ ሥላሴ÷ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን መሠረተ ሃይማኖት እና የካህናት አገልግሎት÷ አዲስ አበባ÷ትንሣኤ ዘጉባዔ ማ/ቤት÷በኔ 21/ 1982 ገጽ 30

[30] ዮሐ. አፈ. ሃይ. አበ. ምዕ 28:36-39



የማዳን ሥራ ጋር የተዋሐደ እንደሆነ እንደ ኖህ መርከብ ለሰው ልጆች የድኅነት መንገድ እንደሆነች ይገልጻሉ::[31]

ቤተክርስቲያኒቱ ማርያም ከልጇ ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ የአማላጅነት ቃል ኪዳን እንደተቀበለችም ታስተምራለች (ዮሐ 2:1-5):: በዮሐ. 19:26 ያለውንም ክፍል ጌታ በመስቀል ላይ ሳለ "እነሆ ልጅሽ" ብሎ ቤተክርስቲያንን ለርሷ፤ "እነሆአት እናትህ" ብሎ እርሷን ለቤተ ክርስቲያን አደራ ሰጥቷል በሚል አንድምታ ትርጓሜ ትረዳዋለች:: እመ አምላክ ÷ ወላዲተ አምላክ መሆኗን አምነው "ስእሊ ለነ ቅድስት" ቅድስት ሆይ ለምኝልን! እያሉ ስሟን የሚጠሩትን ሁሉ እንደሚምርላት የማይለወጥ ኪዳን ተቀብላለች የሚል ትምህርት አላት::[32]

ቤተክርስቲያኒቱ ስለ ማርያም ያላት እምነትም:- "እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርያም ከቅዱሳን ሐዋርያት ሲተላለፍ በመጣው ትውፊት በተገለጠው መሠረት በ64 ዓመት ዕድሜዋ በጥር 21 ቀን ዐርፋለች:: መላእክት ሥጋዋን አሳርገው በገነት በዕፀ ሕይወት ሥር አኖሩአት:: በዚያው ዓመት ሥጋዋ እስከ ነሐሴ 14 ቀን በገነት ከቆየ በኋላ በዚሁ ቀን መላዕክት አምጥተው ለሐዋርያት ሰጡአቸውና በጌተሴማኒ ቀበሩአት÷ በሦስተኛው ቀን ነሐሴ 16 ቀን ተነሥታ በክብር ወደ ሰማይ ዐረገች:: የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ስለ ቅድስት ድንግል ማርያም ዕረፍት÷ ትንሣኤና ዕርገት ይህን ታስተምራለች::

[31] የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት÷ ሥርዓተ ... ገጽ51
[32] ዝኒ ከማሁ÷ ገጽ 52

ታሳምናለች:: በየዓመቱም ነሐሴ 16 ቀን የፍልሰትዋን መታሰቢያ በታላቅ ሥነ ሥርዓት ታከብራለች (ስንክሳር ነሐሴ 16 ቀን)::"[33]

ሠይፈ ሥላሴ የተባሉ የቤተክርስቲያኒቱ ሊቅ ስለ ማርያም አማላጅነት ሲናገሩ:- ድንግል ማርያም የአምላክ እናት እንድትሆን አስቀድሞ በእግዚአብሔር ስለተወሰነ ጥንተ አብሶ ይኑርባት (የክርስቶስ የአድኅኖት ሥራ ለእርሷም ያስፈልግ) እንጂ በአስተሳሰብ፥ በእንደበት፥ በሥራዋም ምንም በደል አልነበረባትም:: ክርስቶስ ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስን በመንሳቱም (በመውሰዱም) የእርሷ ሥጋ ለዓለም የድኅነት መንገድ ሆኗል:: ስለዚህም ታማልዳለች የሚል መከራከሪያን ያቀርባሉ::[34]

### ለ. አቡነ አረጋዊ

ከዘጠኙ ቅዱሳን በጣም ታዋቂና የደብረ ዳሞ ገዳም መሥራች ናቸው:: የደብረ ዳሞ ተራራ ላይ ለመውጣት እየጸለዩ ሳለ ታላቅ እባብ (ዘንዶ) ተልኮላቸው በእፉ በኩል ቢመጣ ጅራቱን እንዲያዞር አዘውት በሰላም የተራራው ጫፍ ላይ መውጣት እንደቻሉ ይተረካል:: እኒህ ሰው በሕይወታቸው ከተከናወኑት ታላላቅ ተዓምራት የተነሣ ቅሩበ እግዚአብሔር ስለሆኑ አማላጃችን ናቸው ብላ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስትያን ታምንባቸዋለች::[35]

[33] ጠቅላይ ቤተ ክህነት፥ *የኢ. ኦ. ተ. ቤተ ክርስቲያን እምነት* ፥ ገጽ 52

[34] *ሠይፈ ሥላሴ፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስትያን መሠረተ ሃይማኖት እና የካህናት አገልግሎት፥ ገጽ. 29-30)::*

[35] Calvin Shenk, "Orthodox Christianity" in *Ethiopian Religion*, p.23



### ሐ. ቅ/ ተክለ ኃይማኖት

እንደ ፕሮፌሰር ታደሠ ታምራት አገላለጽ:- «ተክለ ሐይማኖት በ1208 ዓ/ም ቡልጋ ውስጥ ዞራሬ ሠላሴ ተወለዱ:: ዘሮቻቸው ሸዋ ውስጥ ክእስር ትውልድ በላይ እንደኖሩ ይታመናል:: አባታቸው በሠላሴ ውስጥ በክህነት አገልግሎት የተሰማሩ በመሆኑም የኃይማኖት ትምህርትን እንዳስተማሯቸው፥ ልጅ ሳሉም ግብጻዊው ጳጳስ በዲቁና እንደሾሟቸው ይታመናል::»[36]

አቡነ ተክለ ኃይማኖት የምንኩስና ቆብን ለኢያሱ ሞዓ የሰጡ ቢሆንም ከዚህ አስቀድሞ ግን የሃይማኖትን ቀንበር የተቀበሉት በወሎ ውስጥ በሚገኘው የኃይቅ ገዳም ከራሱ ከእያሱ ሞዓ እንደነበር ይነገራል:: ስለዚህም አቡነ ተክለ ኃይማኖት የእያሱ ሞዓ መንፈሳዊ ልጅ፥ በተወሰነ መጠንም መንፈሳዊ አባት ናቸው:: አቡነ ተክለ ኃይማኖት በሕይወታቸው ማብቂያ ገደማ የደብረ ሊባኖስን ገዳም መሥርተዋል:: ምንም እንኳን የደብረ ሊባኖስ ገዳም በጣም ታዋቂ ቢሆንም ከሐይቅ ገዳም የተገኘ መሆኑ ይነገራል:: አቡነ ተክለ ኃይማኖት በርካታ አስደናቂ ተዓምራትን በአረማውያን፥ በጠንቋዮችና በአስማተኞች መካከል እንደፈጸሙ ይነገራል::[37]

እንዲያውም ዲያብሎስ በዛፍ ባደረበት በካታታ ዛፉን ከእናቱ እያላዘነ (እየጮኸ) እንዲሄድ ቢያዙት ታዟቸዋል ተብሎ ይታመናል:: በሌላ

[36] Tadesse Tamrat, *Church and State in Ethiopia 11270-1527*, Oxford Unverisity Press, 1972, p. 160

[37] Calvin Shenk, "Ethiopian Christianity" in *Ethiopian Religion*, p.23

ጊዜም የአጋንንት ማደሪያ በነበረው በዊፋት ተራራ በሌሊት እሳት ለብሶ በተኩላ እየጋለበና በሌላ እሳት የሚተፋ ተኩላ ታጅቦ የመጣን የአገሬውን አማልእክት በእምነት አባረዋል ይባላል። በየከተማው በርካታ ጣዖታትን ገለባብጠዋል፥ አጋንንት አውጥተዋል፥ ድውያንን ፈውሰዋል፥ ብዙዎችንም ወደ ክርስትና አምጥተዋል የሚልም ትረካ አለ። ስለ አቡነ ተክለ ኃይማኖት ያለው ትውፊትና የክብራቸውን መንስኤ በነጥብ ለማደራጀት ለሞክር እንደሚከተለው ነው፦

1. ከተወለዱበት ዕለት አስቀድሞ ለእያሴ ቀናት የሚያንጸባርቅ ዓምደ ብርሃን በወላጆቻቸው ቤት ላይ እንደታየ ይነገራል።
2. ያጠመቋቸው ቄስ ከቁንጅናቸው የተነሣ ደንግጠው ቢለቋቸው ያልታወቀ እጅ ከሞት እንደታደጋቸው ይነገራል።
3. መነኩሴ በመሆን በኢየሩሳሌም ቅዱሱን መቃብር ጎብኝተዋል፥ በግብጽ ፓትርያርክ በቅስና ተሹመዋል።
4. ቅስና ከተቀበሉ በኋላ ወደ አሮሞ አገር በመምጣት እናታቸውን ከአጋንንት እሥራት ነፃ በማውጣት ብዙ አረማውያንን ወደ ክርስትና አምጥተዋል።
5. ደብረ ዳሞን በጎበኙበት ወቅት በገመድ እየተንተቱ ሳለ ሰይጣን ገመዱን ቢቆርጥባቸው ስድስት ክንፎችን አብቅለው በርረዋል። ስለዚህም በስእላቸው ላይ ክንፍ እንዳላቸው ያሳያል።
6. ሰይጣንን ለአርባ ቀናት አሳምነው እንደ ነበር ይነገራል። ሆኖም ግን እንዴት ተመልሶ ክርስቲያንነቱን እንደተወ ግልጽ አይደለም።
7. ለሰባት ዓመታት በአንድ እግራቸው በሐይቅ ውስጥ ቆመው እግራቸውን አጥተዋል። የእግራቸው ቁራጭ በደብረ ሊባኖስ በየዓመቱ በመፈወሻ ውሃ ይታጠባል። የሚሉቱ ከብዙ በጥቂቱ



የሚወሉ ናቸው።[38] እኝህ ሰው በሕይወታቸው ከተከናወነው ታላላቅ ተዓምራት የተነሣ ቅሩበ እግዚአብሔር በስሆኑ አማላጃችን ናቸው ብላ የኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታምንባቸዋለች።

### መ. ገብረ መንፈስ ቅዱስ

በርካታ ትውፊቶች በእኚህ ጻድቅ ዙሪያ ይተረካሉ። እንደተወለዱ ተነሥተው ቆመው፦ "ክብር ለአብ፥ ክብር ለወልድ፥ ክብር ለመንፈስ ቅዱስ" በማለት ሦስት ጊዜ እንደሰገዱ ይነገራል። በሕይወት ዘመናቸው የእናታቸውን ጡት ወይም ምግብና መጠጥ ወስደው እንደማያውቁም ይታመናል። በሠንጣቃ መሬት (ሸለቋማ ስፍራ) ውስጥ ቢወድቁ ሁለት መላእክት ከሞት አትርፈዋቸዋል፥ በአንድ ወቅት ታላቅ ተራራ እየወጡ ሳለ ሥሳሴ ሊረዷቸው ወርደዋል ተብሉም ይታመናል።

የሞት መልዐክ አይራኤል በሞት ሊወስዳቸው ሲመጣ መብልና መጠጥ ወስጀ አላውቅምና በማለት መሞት እንደሌለባቸው ተናግረው እምቢ ብለዋል፥ በርካታ ቅዱሳን ምድርን ትተው ወደ ሰማይ እንዲሄዱ ቢጠይቋቸውም ተቃውመዋቸዋል፤ መጥምቁ ዮሐንስ፥ ማርያምና ክርስቶስም እንኳ ለምነዋቸው እምቢ ብለዋል ተብሎ ይተረካል።

በመጨረሻም እግዚአብሔር ሳይሞቱ ቢወስዳቸው ከደረቱ አጥንት (rib) እንዷን ለተከታዮቻቸው ጥለውላቸዋል። መቃብራቸው ባለበት

[38] Calvin E. Shenk, “Ethiopian Christianity”, *Ethiopian Religion*, 1970, p. 24

በዛሪኘዋህላ (ሸዋ ውስጥ ነው) የደረት አጥንታቸው ተቀብሮበታል ተብሎ ይታመናል::[39] እኚህ በጻድቅነታቸው ዙሪያ ብዙ የተባለላቸው ሰው በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን በአማላጅነት ተግባር ታላቅ ሚና እንዳላቸው ይታመናል::

በቅዱሳን ስም የሚጻፉት እነዚህ ገድላት ቅዱሳን እግዚአብሔርን እንሞትም ብለው መርታታቸው ብቻ ሳይሆን የሞቱ ነፍሳትንም ከሲዖል እንዳወጡም ይነገርላቸዋል:: በዚህ ጽሑፌ ሂደት ላይ እያለሁ በልጅነቴ ለአባቴ እንደ ጸሎት መጽሐፍ ያነበብኩለት አንድ ገድል ትዝ አለኝ:: ገድለ ክርስቶስ ሰምራ ይባላል:: በታሪኩ ውስጥ ክርስቶስ ሰምራ ሦስት ሺህ ነፍሳትን ከሲዖል እንዳወጣች ይተርካል:: ታሪኩ እንዲህ ነው:- ክርስቶስ ሰምራ አንድ ቀን ሰይጣንንና ክርስቶስን ለማስታረቅ አቅዳ እግዚአብሔርን ታረቅልኝ ብላ ብትለምነው እርሱ እሺ ካለሽ አታረቅልሻለሁ እንዳላትና እርሷም ሲዖል እንደሄደች ያመለክታል::

በዚያ ያጋጠማት ግን ያልጠበቀችው ነገር ነበር:: «ሳጥናኤል» ብላ ብትጠራው በድሮ ስሜ የሚጠራኝ ማን ነው? ብሎ እንደተገረመ፤ ከዚያም እጇን ይዞ አሽቀንጥሮ ቢጥላት እግዚአብሔር መልአኩ ሚካኤልን ወደ ሲዖል እንደላከው ሳጥናኤል ክርስቶስ ሰምራን የሸሸገበትን ስፍራ ለማግኘት ሲል በእርሷ ምክንያት ሦስት ሺህ ሰዎችን ከሲዖል እንዳስወጣ ይተርካል:: ይህንን ገድል ለአባቴ እያነበብኩለት ሳለሁ በአባቴ አዕምሮ በርካታ ጥያቄዎች ተፈጥረውበት ነበር:: አባቴም እያንዳንዱን አንቀጽ ሳነብ እያስቆመኝ:- «ምን ማለትህ ነው? ሰው አይደለችም እንዴ? እግዚአብሔርንና ሰይጣንን ለማስታረቅ ሰው እንዴት

[39] Calvin E. Shenk, "Ethiopian Christianity" in *Ethiopian Religion* p. 24



ይቻላል? መምሬ በቀለ እኮ ዘሮቿን እንደሚያውቁና የቡልጋ ተወላጅ እንደሆነች ሲናገሩ ሰምቻለሁ፤ ይሄ ነገር ቃለ እግዚአብሔር ስመሆኑ ምን ማስረጃ አለ?» የሚሉ ጥያቄዎችን ያቀርብልኝ ነበር:: መቼም በሰውና በእግዚአብሔር መካከል መካከለኛን ለማስገባት ከአዕምሮ በላይ የሆነ ትረካን ማካተት ወሳኝ ነው:: ስለዚህም በጻድቃን ስም በሚጻፉ ጽሑፎች ላይ የእነርሱን ባለገድልነት ለማንጸባረቅ የማይፈነቀል ድንጋይ እንዳልነበረ መረዳት ይቻላል::

### ሠ. ክብረ ዐፅመ ቅዱሳን

ስለ ቅዱሳን ዐፅም ክብር ከማንሳታትን በፊት ቅዱስ ማን ነው? የሚልን ጥያቄ በማንሣት መመልከቱ ወሳኝ ነው:: ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ታሪክና እምነት እንደምንረዳው ቤተክርስቲያኒቱ የተቀበለቻቸውን የሃይማኖት አባቶቿን በሙሉ ከነቢያትና ከሐዋርያት እስከ እንደ ዐፄ ካሌብና ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብ ያሉ ለሰኃይማኖት ጦርነት የከፈቱና በእሳሳች ትምህርት «በመናፍቅነት» የምትቆጥራቸውን ያወደሙትን የሚያካትት ነው:: ታዲያ ታሪካቸውን ከመጽሐፍ ቅዱሱ የቅድስና መመዘኛ ጋር ማነጻጸርን ለአንባቢያን መተው እችል ዘንድ ቅድስና ለእግዚአብሔር መለየት እንደሆነ በማንሳት ወደ ቅዱሳኑ ዐፅም ትውፊት ሳምራችሁ::

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በአማላጅነት የምታምንባቸው በአሁኑ ወቅት በሕይወት እንዳሉ በምታምንባቸው ወይም ደግሞ ሳይሞቱ የተነጠቁ ቅዱሳን ናቸው በምትላቸው ብቻ ሳይሆን ሞትን በቀመሱትም ላይ ነው:: ስለዚህም ቤተክርስቲያኒቱ የጻድቃንና የሰማዕታትን ዐፅም ታከብራለች:: የታላላቅ ገድላት ባለቤት

ወደ ምዕራባውያን የተላከው የርዳታ ጥያቄዋ ምላሽ ዘገየ። ኢትዮጵያ ከዐሥራ አምስት አመታት በላይ በከረመባት የጦርነት እሳት እያሌ ቅርሶቿን አጣች።

እንደ አባ ጎርጎርዮስ አገላለጽ የግራኝ ወረራ ያደረሰው ጉድለት፡- የቤተ ክህነት የሙያ ደረጃ ዝቅ ማለት፤ ያለ ካህን ፈቃድ ማግባት ዕቁባት ማስቀመጥ፤ በሆነ ባልሆነው ሚስት ከባሏ፤ ባል ከሚስቱ መፋታት፤ ከብዙ ሴቶች ብዙ ልጆች መውለድ፤ እንዲሁም የታሪካዊ ቦታዎች ስም በእስላማዊ ስያሜ መለወጡና እንደ ጥሬ ሥጋ መብላት ያሉ ያልተለመዱ የባህል ለውጦች ተጠቃሽ ናቸው። ይህም ያስከተለው ጦስ ከዐሥር አንድ የሚሆኑ አማኞች ብቻ ሃይማኖታቸውን ጠብቀው እንዲገኙ ማድረጉ ነው።[42]

ከዚህም ባሻገር በአምስተኛውና በስድስተኛው መቶ ዓመተ ምሕረት በዓለማችን (በምሥራቃውያን ኦርቶዶክስ እና በምዕራባውያን ካቶሊክ) በመባባል የነበረው የቤተክርስቲያን ክፍፍል የሥነ መለኮት ልዩነትን ያስታከከ የፖለቲካ እንቅስቃሴ የመሆኑን ያህል መሐመድ ግራኝ በተነሣበት ወቅት በኢትዮጵያና በሌሎች ምዕራባውያን መካከል የነበረውም ልዮነት ከእምነት ያፈነገጠ የፖለቲካ ልዩነት ነበር።

በየካቲት 21/1542 ዓ/ም ግራኝ መሐመድ ከተገደለ በኋላ የፖርቹጋል መልዕክተኛ የነበረው ቤርሙዴዝ ለዐፄ ገላውዴዎስ ያቀረበው ጥያቄ አባታቸው ዐፄ ልብነ ድንግል ለፖርቹጋሎች ወሮታ ከኢትዮጵያ መሬት ቆርሰው ለመስጠት ቃል እንደገቡ በማውሳት የተደረገው ጥያቄ

[42] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ 47-48



መመልከት ያሻል፡- «አባትዎ ከአገራቸው ቆርሰው ለፖርቹጋሎች ሊሰጡ ከግብጽ ጳጳስ ማስመጣታችሁም ቀርቶ ከሮም ለማስመጣት፥ በመላዋ ኢትዮጵያ የሮማ ካቶሊክ ሃይማኖት ብሔራዊ እንዲሆን ቃል ገብተውልኝ ነበርና ይህ መፈጸም አለበት። እኔም የመጀመሪያው አቡን ልሁን» እንዳላቸው፤ እሳቸው ግን ጥያቄውን እንዳልተቀበሉት ታሪክ ያስረዳል።[43] እነዚህ ታሪካዊ ክስተቶች በኢትዮጵያ ለእስልምና መስፋፋት የጎላ ድርሻ የነበራቸው ከመሆኑም በላይ እጅግ በጣም ጠቃሚ የሆኑ ንዋየ ቅድሳትንና ታሪካዊ ቅርሶችን ለማጣታችን ምክንያት ሆኗል።

የመሐመዳውያን ተግዳሮት በዚህ ያበቃ አልነበረም። ኢትዮጵያውያን ለእስክንድርያ ቤተክርስቲያን ያላቸውን መስጠት በተለይ ደግሞ ጳጳሳትን ከእስክንድርያ ቤተክርስቲያን የማስመጣት ጥረቷን ተጠቅመው በግብፃውያን ዘንድ ሥር እየሰደደ የሄደውን የእስልምናን ሃይማኖት በኢትዮጵያም የማስፋፋት አቅዳቸውን ገፍተውበት ነበር። ስዚህ እንደ አባ ጎርጎርዮስ አገላለጥ «... አብዱም የሚባል ግብፃዊ እስላም የሐሰት ደብዳቤ ይዞ ወደ ኢትዮጵያ መጥቶ አባ ቄርሎስ ነኝ አለ። የጵጵስና አቀባበል ተደረገለት። ... »[44]

### 1.3.4. ሌሎች ሚስዮናውያንና ተልዕኳቸው በኢትዮጵያ

የፖርቹጊስ-ኢትዮጵያ ግንኙነት በሁለት ዐብይ ሃይማኖቶች አንለባበት ላይ የተመሠረተ ነበር። የመጀመሪያው በ16ኛ ክፍለ ዘመን ኢትዮጵያ

[43] ጠቅላይ ቤተ ክህነት፥የኢት. ኦ. ተ. ቤተ ክርስቲያን እምነት ገጽ 48
[44] አባ ጎርጎርዮስ፥ *የኢትዮጵያ ኦ.ተ.ቤ/ክ ታሪክ*፥ ገጽ 33

በመሐመድ ግራኝ አመራር በሙስሊሞች ጥቃት በደረሰባት ወቅት ነው:: ይህም ንግሥት ሕሊና ወደ ጳጳሱ ወደ ክሊመንት (ቀልመንጦስ) ወደ ፓርቹጋል ለርዳታ እጇን በዘረጋች ወቅት ነበር:: በዐፄ ልብነ ድንግል ዘመነ መንግሥት ምንም እንኳን ንጉሡ የካቶሊካውያኑ ጠቀሜታ ባይታያቸውም የመጀመሪያዎቹ የፖርቹጋል ሚስዮናውያን መጡ::

ሁለተኛው የጀስዊት የካቶሊክ መምጣት ነው:: ይህ ደግሞ አደገኛ የሆነ ችግርን በኢትዮጵያ ላይ አስከትሏል:: ቤርሙድዝ እና ኦፈይደ የተባሉ የካቶሊክ ሚስዮናውያን የእስክንድርያ የኦርቶዶክስ እምነት ተከታይ በነበሩት በንጉስ ገላውዴዎስ እና ከሳቸው ቀጥሎ በነገሡ ነገሥታት ተቀባይነት አላገኙም ነበር:: ከዚህም የተነሣ ካቶሊኮች የሚከተሉትን ጥረቶች ማድረጋቸው ግጭትን አስከተሉ በርካታ ካቶሊካውያን ተገድለዋል በርካቶችም ከአገር ተባረዋል:: ለዚህም በምክንያትነት ከሚጠቀሱት ውስጥ:-

ሀ. ሕዝቡን እንደገና ማጥመቅ መጀመራቸው::
ለ. ግርዘትን መከልከላቸው::
ሐ. አብያተ ክርስቲያናትን እንደገና መባረካቸው::
መ. የሮማውያንን መሠዊያና ምስሎችን ማቆማቸው::
ሠ. ከሮም የጊዜ መቁጠሪያ በማምጣት ማነጻጸራቸው::
ሸ. ቅዳሴውን መቀየራቸው ይገኙበታል::[45]

---

[45] Jones, A.H.M and Elizabeth Monroe, *A History of Ethiopia*, Oxford Univ. Press, 1935 p. 97., See also Calvin Shenk, Eth.Christisnity, in ETR. p. 3



እንደ አባ ጎርጎርዮስ አገላለጽ በ17ኛው ክፍለ ዘመን የካቶሊክ ክርክር ያተኮረባቸው ነጥቦች በገዳም ሕይወትና በነገረ-ክርስቶስ ላይ ነበር:: የፖርቹጋልና የስፓኝ ሚስዮናውያን ብዙ ሕዝብን መለወጥ ችለው ነበር:: ጴጥሮስ ፔሬዝ በመባል የሚታወቀው ሚስዮናዊ ንጉሠ ነገሥት ዐፄ ዘድንግልንና ዐፄ ሡሲንዮስን ካቶሊክ አድርጎ በአጠቃላይ የነገሥታቱ ዘር ላይም ከፍተኛ ተጽዕኖ ፈጥሮ እንደነበርም ይታመናል:: ይሁንና ሕዝቡ በመቃወሙ ምክንያት አልተሳከለትም ነበር፤ እንዲያውም ፖርቹጋሎች ከአገር ተባረው በንጉሥ ፋሲለደስ አማካኝነት መረጋጋት ተችሎአል፥ ብዙ አብያተ ክርስቲያናት፥ የሥነ መስኮትና የያሬዳዊ ሙዚቃ ትምህርት ቤቶች ተመሥርተዋል:: ከካቶሊካውያን መባረር በኋላ የግዕዝ ሥነ ጽሑፍና የሥነ መስኮት መጎልበት ቤተክርስቲያኒቱን ለኢትዮጵያ አንድነት አስተዋጽኦ እንዲኖራት ማስቻሉ ይታመናል::

በዐፄ ፋሲል ዘመነ መንግሥት አልፎንሶ ሜንዴዝ በመባል የሚታወቀውና በ1623 ዓ/ም የኢትዮጵያ ፓትርያርክ እንዲሆን በሮማው ፓፓ በጎርጎርዮስ የተሾመው የእስፓኝ ተወላጅ ለብዙ ሰዎች ደም መፍሰስ በተጠያቂነት ሥር በመዋሉ ከነተከታዮቹ ከአገር እንዲወጣ ቢታዘዝ ፍሬሞና በምትባል ስፍራ ተደብቆ በኢትዮጵያ ላይ በወሰደው የበቀል እርምጃ ቤተክርስቲያኒቱን የሚያተራምስ ትምህርት ስለማስተማሩ አባ ጎርጎርዮስ ሲተርኩ:- "ክብረ ነገሥታችን እንደሚለው አልፎንሶ አሞኛል ብሎ እዚያው ተኝቶ ከጎንደር ተከትለውት መጥተው ለነበሩት ሁለት ኢትዮጵያውያን የቅብዐትንና የጸጋን እምነት

መጥተዋል። በየጊዜው ከስዊድን፥ ከኖርዌይ፥ ከሆላንድና ከጀርመን ብዙ **የፕሮቴስታንት** መልእክተኞች መጥተዋል። ...»[48]

ጀርመናዊው ፒተር ኃይሊንግ ኢትዮጵያን ፕሮቴስታንት ለማድረግ ብቻ ሳይሆን በኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ላይ ጥናት ለማድረግ የመጣ ነበር። የግዕዝ ቋንቋ አውቀቱ የኢትዮጵያን ቤተክርስቲያን ለማጥናትና በተለይ በጎንደር ነዋሪዎች ላይ ተጽዕኖ ማሳደር ቢያስችለውም በምድሪቱ መቆየት እንዳይችል ከሀገር ተባሯል። ይሁንና ትምህርቱ በሕዝብ ልብ ሥፍራ ማግኘቱን መረዳቷ ቤተክርስቲያን የእምነት አንቀጽ በአማርኛ ቋንቋ በማውጣት የመከላከል ጥረት እንድታደርግ አነሣስቷታል።[49]

እንደ ፕሮፌሰር ታደሠ ታምራት ደግሞ:- «በኢትዮጵያ የመጀመሪያው ሚስዮን የቤተክርስቲያን ተልዕኮ ኅብረተሰብ (Church Mission Society) የሚባል ሲሆን ሥራውንም የጀመረው በ1823/24 ዓ/ም በሰሜን ኢትዮጵያ በሳሙኤል ጎባት መሪነት ነው። ይህ ሚስዮናዊና ባልደረቦቹ ከትግራይ ገዢዎች ከሰባጋዲስ ጋር ከ1815-1824 በነበረው ስብሰባ ኢትዮጵያን ለመጎብኘትና ከሕዝቧም ጋር ወዳጅነትን ለመመሥረት ጠቃሚ በሆኑ የእውቀት መስኮችም ሕዝቧን ለማገልገል እንደመጡ ቢገልጹም ስለ ኢትዮጵያ ክርስትና እውነተኛነት ግን ጥያቄ የሞላባቸው ነበሩ። የእርሱ ባልደረባ የነበረው ኩግለር የኢትዮጵያውያን ጸሎተ ፍትሐት ባዶ እና እውነተኛነት የሌለው ሥርዓት ብቻ ነው በማለቱ ትግራይ ውስጥ ሳለ ድንገት እንደ እንደተቀሰፈና የአድዋ መድኃኔዓለም

[48] አባ ጎርጎርዮስ፥ *የኢ.ኦ.ተ. ቤተ ክርስቲያን ታሪክ* ... ገጽ 88-89

[49] Sergaw Hable Selassie and Taddesse Tamrat, Ethiopian Orthodox Church, 1971, p. 37-38



ካህናትም የትግራይ ገዢዎች ስላስገድዷቸው ቤተክርስቲያን ቅጽር ግቢ እንዳይቀበር ከልክለውት ነበር።»[50] የሚል ዘገባም አለ።

### 1.3.5. እንማማር

ቤተክርስቲያን ሁልጊዜ እያንዳንዱ እንቅስቃሴዋን በቃለ እግዚአብሔር መፈተሽ ይኖራባታል። ሁሉም የቤተክርስቲያን መሪዎች ለእግዚአብሔር ያደሩ ናቸው ማለት ካለመቻሉም በላይ በአንድ ወቅት የእግዚአብሔር መንፈስ ያደረበት ሰው ሕይወት የነበራቸው በሌላ ጊዜ ደግሞ የሰይጣን መልእክተኞች ሆነው ሊገኙ ስለሚችሉ በታላቅ ጸሎት ሊታገዙ ይገባል።

በሌላ በኩል ካለፈው የቤተክርስቲያን ታሪክ የምንማረው ለቤተክርስቲያን ተሐድሶ በርካታ መነኮሳት ከግብፅ መጥተው ቅዱሳት መጻሕፍትን የመተርጎማቸውን አስፈላጊነት ነው።

ስለዚህም በእኛም ዘመን ስለቤተ ክርስቲያን ተሐድሶ ስናስብ በሀገራችን ጥንታዊነት ስላላት ቤተክርስቲያን ብቻ ሳይሆን በቅርብ ጊዜ የተተከሉትንም እንደሚመለከትና ለተሐድሶም ወደ ቃለ እግዚአብሔር የመመለስን አስፈላጊነት ልብ ልንል ይገባል። ከዚህ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ነገሥታት አንድን ሰው ወደ ክርስትና ለማምጣት ይጠቀሙበት የነበረው የኃይል እርምጃ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ካለመሆኑም በላይ ምናልባትም አሁን በቤተክርስቲያን ከቃለ እግዚአብሔር ውጪ እንደ ለመስቀል ለሥዕል መስገድ ላሉ ልምምዶች ምንጭ ሊሆን መቻሉ አጠያያቂነት ያለው አይመስለኝም።

[50] አባ ጎርጎርዮስ፥ የኢ.ኦ.ተ. ቤተ ክርስቲያን ታሪክ

በሌላ በኩል ደግሞ የቤተክርስቲያን መሪዎች ከእግዚአብሔር ይልቅ ለምድራዊ ነገሥታት ማደራቸው የመንግሥት ቀኝ እጅነታቸውን አጉልቶ የሚያሳይ የታሪክ ጠባሳ ነው:: ከዚህ ጋር በተያያዘ ደግሞ የቅን ፍርድ መጥፋትን ከማውገዝ ይልቅ ቤተክርስቲያን ጤናማነት ከጎደላቸው የነገሥታት ምግባራት ጋር መስማማቷም በምድር ላይ የመኖሯን ዓላማ አጠያያቂ አድርጎታል:: ስለዚህም ቤተክርስቲያን ለእግዚአብሔር እውነት ጠበቃ በመሆን መንግሥታት ሲስቱ ለመመለስ መነሣት ይኖርባታል:: ከዚህ በተጨማሪ ደግሞ ክፍፍልን ከሚያካርሩና ቂመኝነትን ከሚያሳድጉ ተግባራት የመታቀብ አስፈላጊነትም ጎልቶ መታየት አለበት::

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን የምልጃ ትምህርትን በተመለከተ የጌታችን እናት የቅድስት ማርያም አማላጅነት መሠረት በወንጌል ዮሐንስ ምዕራፍ 2 እና 19 ክርስቶስ ለሰው ልጆች የመስቀል ሞት ጽዋን ከመቀበሉ በፊት ከተጠቀሱትና በአተረጓጎም ልዩነት ከተንጸባረቀባቸው ሁለት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች ይልቅ በገድል ላይ ነው:: በአማላጅነት ዙሪያ ለመማማር ይቻል ዘንድ አስቀድሞ የምልጃን ፅንሰ ሐሳብ መመልከቱ አስፈላጊ ነው::

የምልጃ ፅንሰ ሃሳብ በተለይ በሀገራችን ታሪክ በሥልጣን ላይ ያሉትን በቀጥታ መቅረብ እንደ ንቀትና ነውር ተደርጎ ስለሚቆጠር ለባለሥልጣኑ የላቀ ቀረቤታ ባለው ሰው አማካኝነት ካልሆነ በቀር በቀጥታ መቅረብ ካለመቻሉ ጋር በታያያዘ ለመሆኑ ታሪክ ያስረዳናል:: ስለዚህም በነገሥታትና በሕዝባቸው መካከል ከፍተኛ አርከን አለ:: ለንጉሡ አቤቱታን ለማቅረብም ሆነ ከንጉሡ ምሕረትን ለመቀበል ደረጃውን



ጠብቆ በንጉሥ ባለሟሎች አማላጅነት ካልሆነ በቀር በቀጥታ በፍጹም የማይቻል ነበር::

ይህንን እሳቤ ይዞ ወደ መጽሐፍ ቅዱስ የመምጣት ውጤቱ ደግሞ እግዚአብሔርን የሚያክል የዓለም ሁሉ ፈጣሪ የሆነ አምላክማ እንዴት በቀጥታ ሊቀረብ ይቻላል? ወደሚል ድምዳሜ ማድረሱ አይቀሬ ነው:: በዚህ እሳቤ ላይ ተንተርሶ ወደ ሥነ መለኮት ትምህርት ከተቀረበ ደግሞ የጌታችንን እናት ማርያምን ቀርቶ ከጆሐድ እሳቤ ባልተናነሰ በአመለካከታቸው ልዩነት የሰው ልጆችን ምላስ ቆርጠ በድንጋይ ተወግረው እንዲሞቱ ያደረገ ዐፄ ዘርዓ ያዕቆብንም ከአማላጅ ተርታ ከመመደብ አለመመለሱ አጠያያቂ አይደለም::

የጌታችን እናት ቅድስት ማርያም የጸጋ ስግደት (አክብሮት) የተገባት መሆኑ የልዩነት መሠረት ተደርጎ መቆጠር የሚችል አይመስለኝም:: ችግሩ ግን በጸጋና በአምልኮ ሥግደት መካከል ያለውን ልዩነት ማስመር አለመቻሉ ላይ ነው:: እንዲያው ለመሆኑ በኢትዮጵያ በጻድቃን ስም እየተፈጸሙ ያሉ ሃይማኖታዊ ልምምዶች አክብሮት ወይስ አምልኮ? ለዚህ ጥያቄ መልሱ ግልጽ ነው:: ታዲያ ለምን እንሸነጋገላለን? የምናታልለውስ ማንን ነው?

ሌላው ደግሞ ክርስቶስ ከእናቱ ከማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷም ነፍስ እንደነሣ በማተት ለአማላጅነት መሠረት አድርጎ ለማቅረብ መሞከርን በተመለከተ ነው:: በመጀመሪያ ደረጃ ሕፃን ሲፀነስ ከእናቱና ከአባቱ ሥጋና ነፍስ ይነሳል (ይወስዳል) የሚለው አመለካከት በኢትዮጵያ ጥንታዊነት ይኑረው እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊም ሆነ ሳይንሳዊ ማስረጃን ማቅረብ ፈጽሞ የማይቻል ነው:: ከዚህ በተጨማሪም

ክርስቶስ የማርያም ልጅ በመሆኑ የእርሱ ሥጋ የእርሷ ሥጋ ስለሆነ እሷ እድኅኖተ ሰብ (ቤዛዊተ ዓለም) ናት ማለትም እመክንዮታዊነት የሚጎድለውና ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነት ሳይሆን ከላይ ከተገለጸው የፍልስፍና እሳቤ የመነጨ መሆኑ ግልጽ ነው።

የጻድቃንን አማላጅነት በተመለከተ የተነሣው መከራከሪያም በቅዱሳኑ እንደተፈጸሙ በሚነገሩ ተዓምራት ላይ ነው። የቅዱሳን ገድል ተደርገው ከሚነገሩት ውስጥ:- የአቡነ ተክለ ኃይማኖት ዛፍን እየጮኸ እንዲሄድ ማዘዝ፥ ክንፍ አብቅሎ መብረርና ሰይጣንን ለ40 ቀናት ማሳመናቸው፤ የአቡነ ገብረ መንፈስ ቅዱስ ክርስቶስ እንኳ እንዲሞቱ ቢለምናቸው አልሞትም ማለታቸው ከመጽሐፍ ቅዱስ ትምሕርት ጋር መጣረሉ ሳይታለም የተፈታ ነው። ክርስቶስ ለምራም ሰይጣንንና እግዚአብሔርን ለማስታረቅ እንኳን መሞከሩዋ ማለቧም ከመጽሐፍ ቅዱስ እውነታ ጋር የሚቃረን ነው። ምክንያቱም የሰይጣን ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ የእግዚአብሔር እቅድ ቢሆን ኖሮ የሰው ልጆችን ከራሱ ጋር ለማስታረቅ ከድንግል ማርያም የተወለደው ጌታ ቢያስፈልግ ሁለተኛ ጊዜ ደግሞ ለሰይጣን ይሞትለት ነበር።

ይባስ ብሎ በሕይወት ዘመናቸው የክርስቶስን ጽድቅ በእምነት ጽድቃቸው ባለማድረጋቸው ሲዖል የገቡ ሰዎች ከሲዖል የመውጣት ጉዳይ በእግዚአብሔር እውነት ላይ የሚነሳ የሠይጣን አሳሳች አሠራር ስመሆኑ ጥርጥር የለውም። ምክንያቱም በሉቃስ ወንጌል ምዕራፍ 16 ቁጥር 19-26 ላይ ባለጠጋው ሰው በሞተ ጊዜ በምድር ሳለ እደጃፉ ይተኛ የነበረ አልዓዛር የሚባል ሰው ከሞተ በኋላ እሻግሮ በአብርሃም እቅፍ ያየዋል። በዚህም ጊዜ ለአብርሃም:- የጣቱን ጫፍ ነክሮ መላሴን



እንዲያበርድልኝ አልዓዛርን ስደድልኝ ብሎ ቢጠይቀው የአብርሃም ምላሽ:- «- - - ከዚህም ሁሉ ጋር ከዚህ ወደ እናንተ ሊያልፉ የሚፈልጉ እንዳይችሉ፥ ወዲያ ያሉ ደግሞ ወደ እኛ እንዳይሻገሩ በእኛና በእናንተ መካከል ታላቅ ገደል ተደርጎአል አለ።» ይለናል።

እንግዲህ ይህ የእግዚአብሔር እውነት የሚያስረዳን የእምነት አባታችን የሆነው አብርሃም ከሞት በኋላ እንኳን በመካከላችን ገደል ተደርጎአል የሚል ከሆነ፤ የእኛዋ ጻድቅ ለ3000 ነፍሳት ከሲዖል መውጣት ምክንያት የሆነችበት ምን ይሆን? ከዚህም በተጨማሪ ለወንጌላዊው ሉቃስ ያልተገለጠ የእግዚአብሔር እውነት ለገድለ ክርስቶስ ሰምራ ደራሲ እንዴት ተገለጠ? ይህ ይሆናል ብሎ ማመን ደግሞ ከወንጌል እውነት በተቃራኒ ለመሐመድም እንደተገለጠ ከማመን የማይመለስ በመሆኑ የሃይማኖት ብሬ ለማንሳት ወደ መሞከር ፈቀቅ ያለ ነው።

እንደ እነዚህ ያሉና በቅዱሳን ስም በገድልነት ለተዘጋጁ መጻሕፍት የቤተክርስቲያኒቱ ሊቃውንት በወንጌል ላይ እያሳደሩ ያለውን ተጽእኖ ለማስወገድና የክርስቶስ ሐዋርያዊ ተልዕኮን ለመወጣት ቆራጦች መሆን ይጠበቅባቸዋል። ለዚህ ችግር እንደ መፍትሄ የማቀርበው በታሪክ ሂደት የተፈጠረን ታላቅ ስህተት ለማረምና ለተሐድሶ በተከፈተ ልብ መነሣትን ነው። ለሃይማኖት ትምህርት መሠረት የማይሆኑና ኢትዮጵያውያን ሆነው ሳሉ ሕዝባቸውን ከወንጌል እውነት ውጭ በማድረግ ምሕረት የሌለው ሐጢአት የተዘፈቁ የገድል ደራሲያን ውዥምብር ሳንደናገር ለክርስቶስ ወንጌል ሰፍራውን ብናስለቅቅ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ተግባር መሆኑ ግልጽ ነው።

እንደ አባ ጎርጎርዮስ አገላለጽ ዝክረ-ሊቃውንት በሚባል መጽሐፋቸው መልእከ ብርሃን እድማሉ ጀምበሬ የጻፉትን በመጥቀስ፤ በቦሩ ሜዳ ጉባኤ በተዋሕዶዎችና በጸጎች መካከል በተደረገ ክርክር ወቅት ለጸጎች ተወካይ ለአለቃ ሥነ ጊዮርጊስ ምላሽ የሰጡትን ዳኝነት ስንመለከት፡- «ዓፄ ዮሐንስም ነገሩ እንዳላማረ አዩትና ተጠየቁ ቀርቶ ወልደ ዮሐንስ ሁለት ልደት የሚል ምስክር ከመጽሐፍ እንዳመጣ አንተም ሦስት ልደት የሚል ደረቅ ንባብ አምጣ አሏቸው፡፡ አለቃ ሥነ ጊዮርጊስም በደብረ ብርሃን ተአምረ ማርያም ተጽፏል አሉ፡፡ ከምታስተምረው ከአራቱ ጉባዔ አጣህና ስለ ሃይማኖት ተአምረ ማርያም ትጠቅሳለህን? ቢሏቸው ከጉባኤው መጽሐፍስ የለም አሉ፡፡...»[51]

ከዚህ የምንረዳው ስለ ሃይማኖት ከመጽሐፉ፥ ደረቅ ንባብ እና ከአራቱ ጉባኤ በሚል የሥነ መለኮት ክርክር የዳኝነት መስፈርት እንደነበር ነው፡፡ ይህም ተዓምረ ማርያም ለሃይማኖት ትምህርት መጠቀስ እንደሌለበትም አመላካች ነው፡፡ በዚህ ዘመን ግን በርካታ ሃይማኖታዊ እሳቤዎች በዚህ የዳኝነት መስፈርት ሳይፈተሹ መሰበካቸው ከቃለ እግዚአብሔር ለሚቃረን አስተምህሮት ምንጭ ሆኗል፡፡ ስለዚህም ሥር እየሰደደና ቤተክርስቲያንን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ እያደረጋት ያለ አካሄድ በጊዜ መታረሙ አጠያያቂነት አይኖረውም፡፡

የመሐመዳዊያንን ተግዳሮትነት በተመለከተም ቤተክርስቲያን እንድነት የማጣቷ ጦስ በመሆኑ ልንማማርበት የተገባ ነው፡፡ ቤተክርስቲያን በአረማዊነት ባህል ለመወረሷና እንደ ድርብ ጋብቻ ያሉ ኢ-ክርስቲያናዊ

---

[51] አባ ጎርጎርዮስ፥ የኢ.ኦ.ተ.ቤ.ክ.ታሪክ፥ ገጽ. 72



ምግባራት መስፋፋት ተጠቃሹ እስልምና በኢትዮጵያ ያደረሰው ተፅዕኖ ቢሆንም ለዚህ አይነቱ ምግባር መስፋፋት ንጹሑን ወንጌል ባለመስበኳና የአማኞች የሕይወት ለውጥ ማምጣት የሚችል ትጋት ባለማንጸባረቃቸው የቤተክርስቲያን አባቶች ተወቃሾች ናቸው፡፡

የካቶሊክ ሚስዮናውያንን ተግዳሮትም በተመለከተ በተለይ ከጀስዊት (ኢየሱሳውያን) ሚስዮናውያን ውድቀቶች የምንማራቸው ሦስት መሠረታዊ ነገሮች፡-

ሀ. የሃይማኖት ቀኝ ግዛትን ለማስፋፋት ከመሞከር ይልቅ ኢትዮጵያዊ የካቶሊክ ቤተክርስትያን አለመትከላቸው፡፡

ለ. በአስተምህሮት ሙግት መጠመዳቸው፡፡

ሐ. የሕዝቡን ወግ መጣሳቸውና ጣልቃ ገብነትን መፈጸማቸው ለእግዚአብሔር መንግሥት የማይጠቅም በያዙት ዓላማም ውጤታማነትን የማያቀዳጅ መሆኑን ነው፡፡

በኢትዮጵያ ምድር ወንጌልን ከገድላት ጥቃት ለመከላከልና ከወንጌል መሠረታዊ እውነት ውጪ የሚነሱትን የመናፍቅነት ትምህርቶች ለመከላከል ቀዳሚ ስፍራ ያላቸው የፕሮቴስታንት ሚስዮናውያን ሳይሆኑ በዐፄ ዘርዓ ያቆብ ዘመን የተነሱ እነ አባ እስጢፋኖስ እንደ ነበሩ ከታሪክ መረዳት ይቻላል፡፡ ሆኖም ግን በንጉሡ ትዕዛዝ ጭከና በሞላበት መንገድ ሕይወታቸውን አጥተዋል፡፡ ከዓመታት በኋላም በኢትዮጵያ ምድር ሰብከተ ወንጌልን ያለ ባህል ግጭትና በአገሬው እውድ የዳበረውን የነገረ-ክርስቶስ አስተምህሮ ሳያፋልሱ ለማስፋፋት መልካም ምሳሌነት እንዳላቸው ከሚመሰከርላቸው ሚስዮናውያን ውስጥ ፒተር ኃይሊንግ አንዱ ናቸው፡፡ እንደ እድማሱ አገላለጽ የዚህ የጸጋ ልጅ ትምህርት ምንጩ ካቶሊክ እንጂ የፕሮቴስታንቱ ፒተር ኃይሊንግ እንዳይደለ ነገር

ግን የፕሮቴስታንቶች ሚሲዮንማ "እመን ብቻ ትድናለህ!" የሚልን ስብከት እንደ ባንድራ ከማንገብ ውጪ ለፀጋ ልጅ ትምህርት መንስዔ አይደሉም የሚልን ሃሳብ አንጸባርቀዋል::[52]

ይህ ደግሞ ከወንጌል ተልዕኮ አንጻር ጥልቅ ምርመራን ያዘለ (የሒስ) አውዳዊነትን (Critical Contextualization) የሚጠይቅ ነው:: ስለሆነም ይህ አውዳዊነትን ያተኮረ ተልዕኮን የመወጣት ስልት ግጭትንና ውዝግብን በማነሳሳት ለፖለቲከኞች መጠቀሚያ ሳይሆን በወንጌል ሥርጭት መስክ የተሰማሩ አገልጋዮች የማዳንን እውነት በማይበርዝና በማይሸቅጥ መንገድ በአገሬው አውድ የማቅረብ ውጤታማነት እንዲኖራቸው ስለሚያስችል ከቀደምት የካቶሊክ ሚሲዮናውያን ውድቀትና ከፕሮቴስታንቱ ሚሲዮናዊ ከፒተር ኃይሲንግ ተልዕኮ ተኮር አውዳዊነት የምንማረው ታላቅ ትምህርት አለን::

[52] Tesfazghi Uqbit, *Current Christological Positions of E.O.C Theologians*, p.68-69



## II. የክርስትና መሠረት ስለሆኑ መጻሕፍት የምንማማረው

### 2.1. ቅዱሳት መጻሕፍት በተዋሕዶ ግንዛቤ

ቅዱሳት መጻሕፍት በሁለት ማለትም በብሉይና በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትነት ተለይተው ይገለጻሉ:: በተለይ ለብሉይ ኪዳን መጻሕፍት አይሁድ የመጀመሪያ የመጻሕፍቱ ተቀባዮች በመሆናቸውና የትኞቹ ነቢያት ከእግዚአብሔር ጋር ትክክለኛ ግንኙነት የነበራቸው እንደሆኑ ባላቸው መረዳት ላይ በመመስረት ቅዱሳት መጻሕፍትን ለይተው ነበር:: ቤተክርስቲያንም የትኞቹ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ቅዱሳት መጻሕፍት እንደሆኑ ለይቶ በማውጣት ረገድ በአይሁድ ዘንድ ተቀባይነት ያገኙትን መጻሕፍት ከመቀበልና እነርሱ ያልተቀበሏቸውንም ከመቀበል አንጻር ልዩነቶች ተከስተዋል::

በአይሁድ ዘንድ ነቢያቱ ከእግዚአብሔር መሆናቸው የታመነባቸውና በቃለ እግዚአብሔርነት ተቀባይነት ያላቸው መጻሕፍት ብዛት ሃያ አራት ናቸው:: ጆሴፈስ እነዚህኑ ሃያ አራት መጻሕፍት ወደ ሃያ ሁለት ዝቅ ያደርጋቸዋል:: በታሪክ ዘጋቢነቱ በሚታወቀው በጆሴፈስ አደረጃጀት መጽሐፈ ሩትን ከመጽሐፈ መሳፍንት ጋር፤ ሰቆቃው ኤርምያስን ከትንቢተ ኤርምያስ ጋር በማቆራኘት በሁለት ቁጥሮች እንዲቀንስ በማድረግ ነው:: የመጻሕፍቱ ቅደም ተከተልም ሆነ በቡድን ያላቸው አደረጃጀት የተለየ ነው::[53]

[53] F.F. Bruce, *The Canon of Scripture*, p. 33

በአይሁድ ባህላዊ አደረጃጀት መሠረት እነዚህ ሃያ አራቱ የአይሁድ ቅዱሳት መጻሕፍት በሦስት ቡድኖች ተከፋፍለዋል፡- የሕግ መጻሕፍት (ቶራ) የትንቢት መጻሕፍት (ነቢም) እና ጽሑፎች (ኬቱቢም) በመባል ይታወቃሉ፡፡ በሕግ መጻሕፍት ሥር አምስቱ የሙሴ መጻሕፍት በመባል የሚታወቁትን፡- ኦሪት ዘፍጥረት፥ ዘጸዐት፥ ዘኁልቁ፥ ዘሌዋውያንና ዘዳግም ናቸው፡፡ እነዚህ እስራኤላውያን ከባቢሎን ምርኮ እንደተመለሱ የመጀመሪያ የቀኖና መጻሕፍት ናቸው፡፡

የትንቢት መጻሕፍትን በሁለት በመክፈል ቀዳሚ ነቢያት(Former Prophets) እና የኋለኞች ነቢያት (Latter Prophets) መጻሕፍት ይሏቸዋል፡፡ በቀደምት ነቢያት መጻሕፍትነት የሚዘረዝሩዋቸው መጻሕፍት፡- መጽሐፈ ኢያሱ፥ መሳፍንት፥ ሳሙኤል እና ነገሥት ሲሆኑ የኋለኞች ነቢያት መጻሕፍት በመባል የሚጠሩቱ ደግሞ፡- ኢሳይያስ ኤርምያስ ሕዝቅኤልና አሥራ ሁለቱ የደቂቅ ነቢያት መጻሕፍት ናቸው፡፡ እነዚህ መጻሕፍት የቀኖና መጻሕፍት የሆኑት ከሕግ መጻሕፍት ቀጥለው ከክርስቶስ ልደት በፊት በሦስተኛው ምዕተ ዓመት ማገባደጃ ላይ ነው፡፡

በጽሑፎች ሥር የሚዘረዘሩት መጻሕፍት ደግሞ የግጥም መጻሕፍት፡- መዝሙረ ዳዊት፥ መጽሐፈ ምሳሌ፥ ኢዮብ በመቀጠልም አምስት መጻሕፍትን የሚያካትት (Megillot) በመባል የሚታወቁ መጻሕፍት፡- መኃልየ መኃልይ፥ ሩት፥ ሰቆቃወ ኤርምያስ፥ መክብብ እና አስቴር በመጨረሻም በታሪክ መጻሕፍትነት የሚጠቀሱ፡- ዳንኤል፥ ዕዝራ-ነህምያ (እንደ አንድ መጽሐፍ ተቆጥረው) እና መጽሐፈ ዜና



ናቸው፡፡ የዕብራውያን መጽሐፍ ቅዱስ በህትመት ጥራዝ ያለውም ቅደም ተከተል ከላይ በተዘረዘረው መሠረት ነው፡፡[54]

እነዚህ መጻሕፍት በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ሠላሳ ዘጠኙ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በመባል የሚታወቁቱ ራሳቸው ሲሆኑ የቤተክርስቲያን አባቶች ለአጠቃቀም እመቹ ናቸው ብለው በማመናቸው እንዳንዶቹን መጻሕፍት ለሁለት በመከፈል አንደኛና ሁለተኛ በማለት ቁጥራቸውን ሠላሳ ዘጠኝ አድርሰውታል፡፡ የቅደም ተከተልና በቡድን የማደራጀት ለውጦችም ተንጸባርቆበታል፡፡ በቤተክርስትያን አባቶች ባህላዊ አደረጃጀት መሠረት የሕግ፥ የታሪክ፥ የጥበብ (የቅኔ) እና የትንቢት መጻሕፍት በመባል በአራት የተከፈሉት እነዚሁ መጻሕፍት ናቸው፡፡

ከአደረጃጀቱ ልዩነትም ውስጥ በአይሁድ ዘንድ በቀዳሚ ነቢያት መጻሕፍትነት የሚጠቀሱቱ በክርስቲያኖች ባህላዊ አጀረጃጀት የታሪክ መጻሕፍት ውስጥ መካተታቸው! ትንቢተ ዳንኤል በመባል በክርስቲያኖች ባህላዊ አደረጃጀት በትንቢት መጻሕፍት ቡድን ውስጥ የተካተተው በአይሁድ ዘንድ በጽሑፎች ሥር የታሪክ መጽሐፍ ተደርጎ መቦደኑ ተጠቃሽ ነው፡፡ በክርስቲያኖች ባህላዊ አደረጃጀት ትንቢተ ሚልክያስ የመጨረሻው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ሲሆን በአይሁድ ባህላዊ አደረጃጀት ግን መጽሐፈ ዜና የመጨረሻው መጽሐፍ ነው፡፡ ምንም እንኳን በብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ረገድ ከአይሁድ መጻሕፍት ጋር በማነጻጸር መመልከታችን አስፈላጊ ቢሆንም በአዲስ ኪዳን መጻሕፍት አንጻር ግን ስለ አይሁድ ማንሣት አያስችለንም፡፡ ለዚህም ዋናው

[54] F.F. Bruce, *The Canon of Scripture*, p. 29

ምክንያት ደግሞ አይሁድ የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትን በአጠቃላይ በቃለ እግዚአብሔርነት የማይቀበሉ በመሆኑ ነው::

በአጠቃላይ መልኩ ከተመለከትነው ከቀኖናዊ መጻሕፍት ውጪ ያሉቱ ሁለት ዓይነት ናቸው:- አንደኛዎቹ የአዋልድ መጻሕፍት (Apocrypha) በመባል የሚታወቅ ሲሆን አማኞችን የሚያንጹ! ነገር ግን እስትንፋሰ እግዚአብሔር ያለባቸው ለመሆኑ ያልታመነባቸው ናቸው:: ሁለተኛዎቹ ደግሞ በብሉይ ኪዳንም ሆነ በአዋልድ መጻሕፋት ውስጥ የማይካተቱ ተዓማኒነት የሌላቸው (Pseudepigrapha) ናቸው::

### 2.1.1. የቀኖና መጻሕፍት

ስለ ቀኖና መጻሕፍት ከማንሣቴ በፊት የቀኖናን ምንነት መግለጽ አስፈላጊ ነው:: ቀኖና የሚለው ቃል ከግሪኩ ቃል κανων (ካኖን) የተገኘ ሲሆን ጥሬ ትርጉሙም መለኪያ፥ ዘንግ ወይም ሥርዓት ማለት ነው:: በቅዱሳት መጻሕፍትነት ከታለቡት ውስጥ የትኞቹ መጻሕፍት ቃለ እግዚአብሔር በመሆናቸው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ መካተት የሚያስችላቸውን መስፈርት እንደሚያሟሉ ተለይተው የወጡበት መንገድ ነው:: ስለዚህም ይህ ቃል በእውነተኛነት እና በእምነት መለኪያነት ትርጓሜም በቤተ ክርስቲያን ጥቅም ላይ ውሏል::

ከላይ በተደረገው ገለጻ ላይ በመመርኮዝ የትኞቹ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ለክርስትና እምነት መሠረትና የሕይወት መመሪያ እንደሆኑ ለይተው በማውጣት ረገድ የቤተ ክርስቲያን አባቶች የጎላ አስተዋጽኦ



ነበራቸው:: በአጠቃላይ የክርስቲያኖች ዓለም የቀኖና መጻሕፍት በመባል የሚታወቁ ሠላሳ ዘጠኝ የብሉይ ሃያ ሰባት የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት እሉ::

### 2.1.2. ዳግማዊ የቀኖና መጻሕፍት (Deutro-Canonical Books)

#### 2.1.2.1. የብሉይ ኪዳን ዳግማዊ የቀኖና መጻሕፍት

ደግማዊ የቀኖና መጻሕፍት ወይም የብሉይ ኪዳን 2ኛ መጻሕፍት በመባል የሚታወቁት በአጠቃላይ በክርስቲያኖች ዘንድ ተቀባይነት ካላቸው ከ39ኙ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በተጨማሪነት በተለያዩ ቤተ-እምነቶች ተቀባይነት የሌላቸው መጻሕፍት ናቸው:: እነዚህ በካቶሊክም ሆነ በኦርቶዶክ አብያተ ክርስቲያናት ዘንድ በጋራ ተቀባይነት ያላቸው መጻሕፍት የመኖራቸውን ያህል አንዳንዶቹ መጻሕፍት እስትንፋሰ እግዚአብሔር ባይኖርባቸውም በታሪክ መጻሕፍነታቸው እንዲሁም የአዋልዳዊ ሥነ ጽሑፍን ባሕርያት ለማጥናት ጥቅም ላይ ይውላሉ::

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ተቀባይነት ያላቸው ዳግማዊ የቀኖና መጻሕፍት ታሪካዊ ዳራ ከ13ኛው መቶ ዓመተ ምሕረት ጋር በተያያዘ እንደሆነ የሚነገር ሲሆን ሁለት የተለያዩ ቀኖናዎችም ይንጸባረቃሉ:: እነዚህንም ሰፊ ቀኖናና ጠባብ ቀኖና በማለት ለመክፈል በመሞከር ለያይቶ መመልከቱ አስፈላጊ ነው::

ከሰፊው ቀኖና በመጀመር ስንመለከት በዚህ ቀኖና መሠረት 81 መጻሕፍት የሚካተቱ ሲሆን ከአነዚህም ውስጥ 46ቱ የብሉይ ኪዳን፥ 35ቱ ደግሞ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ናቸው:: የብሉይ ኪዳን 46ቱ

መጻሕፍት ዝርዝር በቀኖና መጻሕፍት እና በዳግማዊ የቀኖና መጻሕፍት አደረጃጀት ሲዘረዘሩ የሚከተሉት ናቸው[55]:-

ሀ. የብሉይ ኪዳን የቀኖና መጻሕፍት

1. ኦሪት ዘፍጥረት
2. ኦሪት ዘጸአት
3. ኦሪት ዘሌዋውያን
4. ኦሪት ዘኍልቊ
5. ኦሪት ዘዳግም
6. መጽሐፈ ኢያሱ
7. መጽሐፈ መሳፍንት
8. መጽሐፈ ሩት
9. 1ኛና 2ኛ ሳሙኤል
10 1ኛና 2ኛ መጽሐፈ ነገሥት
11. 1ኛ መጽሐፈ ዜና መዋዕል
12. 2ኛ መጽሐፈ ዜና መዋዕል
13. መጽሐፈ ዕዝራና ነህምያ
14. መጽሐፈ አስቴር
15. መጽሐፈ ኢዮብ
16. መዝሙረ ዳዊት
17. መጽሐፈ ምሳሌ (ከምዕራፍ 1-24)
18. መጽሐፈ ተግሣጽ (ምሳሌ ምዕራፍ. 25-31)
19. መጽሐፈ መክብብ
20. መጽሐፈ መኃልየ መኃልይ

---

[55] ጠቅላይ ቤተ ክህነት÷የኢ. ኦ. ተ. ቤ/ክ እምነት ሥ. አምልኮና... ገጽ 42-43



21. ትንቢተ ኢሳይያስ
22. ትንቢተ ኤርምያስ (ሰቆቃው ኤርምያስን ያካትታል)
23. ትንቢተ ሕዝቅኤል
24. ትንቢተ ዳንኤል
25. ትንቢተ ሆሴዕ
26. ትንቢተ አሞጽ
27. ትንቢተ ሚክያስ
28. ትንቢተ ኢዩኤል
29. ትንቢተ ዐብድዩ
30. ትንቢተ ዮናስ
31. ትንቢተ ናሆም
32. ትንቢተ ዕንባቆም
33. ትንቢተ ሶፎንያስ
34. ትንቢተ ሐጌ
35. ትንቢተ ዘካርያስ
36. ትንቢተ ሚልክያስ

ለ. <u>የብሉይ ኪዳን ዳግማዊ የቀኖና መጻሕፍት</u>

1. መጽሐፈ ኩፋሌ
2. መጽሐፈ ሄኖክ
3. ዕዝራ ካልዕና ዕዝራ ሱቱኤል
4. መጽሐፈ ጦቢያ (ት)
5. መጽሐፈ ዮዲት
6. መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ
7. 2ኛና 3ኛ መጽሐፈ መቃብያን
8. መጽሐፈ ጥበብ

9. መጽሐፈ ሲራክ

10.መጽሐፈ ዮሴፍ ወልደ ኮርዮን

- በአጠቃላይ ድምራቸው 46 ነው::

ማስታወሻ:- ቁጥራቸው ከሠላሳ ዘጠኝ ወደ ሠላሳ ስድስት የቀነሰበት ምክንያት አራት መጻሕፍት በመጣመራቸው፤ ምሳሌ ተግሣጽ ደግሞ ከመጽሐፈ ምሳሌ ተከፍሎ ሰብቻው በመውጣቱ ነው እንጂ ከቀኖና መጻሕፍት ውስጥ የማትቀበላቸው መጻሕፍት በመኖሩ እንዳይደለ ማስተዋል ያሻል::

ከጠባቡ ቀኖና አንጻር ከተመለከትነው ደግሞ በአጠቃላይ የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ብዛ ቸው 81 ሲሆኑ 54ቱ የበሉይ 27ቱ ደግሞ የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት እንደሆኑ መመልከት ይቻላል:: የቀኖና መጻሕፍትን በተመለከተ በሌሎች ዘንድ ተቀባይነት ያላቸውን 39ኙን መጻሕፍት ሙሉ ለሙሉ የምትቀበል ሲሆን ብዛ ቸውን በተመለከተ ግን ከመጽሐፈ ምሳሌ ምዕራፍ 25-31 ያለውን መጽሐፈ ተግሣጽ በሚለው ስያሜው ሰብቻው በማቅረብ ዐርባ መጻሕፍት ናቸው ትላለች:: ከእነዚህ በተጨማሪ የሚከተሉት የብሉይ ኪዳን ዳግማዊ የቀኖና መጻሕፍት ይካተቱበታል[56]:-

የብሉይ ኪዳን 2ኛ (ዳግማዊ) የቀኖና መጻሕፍት

| | |
|---|---|
| መጽሐፈ ዕዝራ ሱቱኤል | ጸሎተ ምናሴ |
| መጽሐፈ ዕዝራ ካልዕ | ተረፈ ኤርምያስ |
| መጽሐፈ ጦቢት | ሶስና |

[56] መጽሐፍ ቅዱስ: የብሉይና የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት (በኢ. ኦ. ተ. ቤተ ክርስቲያን የታተመ)፥ በ1980 ዓ/ም



| | |
|---|---|
| መጽሐፈ ዮዲት | መጽሐፈ ባሮክ |
| መጽሐፈ አስቴር | መጽሐፈ ጥበብ |
| (ከቀኖናው መጽሐፍ ሌላ) | |
| መጽሐፈ መቃብያን ቀዳማዊ | መዝሙረ ሠለስቱ ደቂቅ |
| መጽሐፈ መቃብያን ካልዕ | ተረፈ ዳንኤል |
| መጽሐፈ መቃብያን ሣልስ | መጽሐፈ ኩፋሌ |
| መጽሐፈ ሲራክ | መጽሐፈ ሄኖክ |

የእነዚህ መጻሕፍት ብዛት 18 ሲሆን ተረፈ ኤርምያስንና ተረፈ ዳንኤልን ለትንቢተ ኤርምያስና ለትንቢተ ዳንኤል በተጨማሪነት ከተያዙና መጽሐፈ ተግሣጽም ከመጽሐፈ ምሳሌ ጋራ ከተቆጠረ እንዲሁም ሌላው መጽሐፈ አስቴር ከቀኖናው መጽሐፈ አስቴር ጋራ ከተቀናጀ ከላይ ከተዘረዘሩት የቀኖና መጻሕፍት ጋር በጠቅላላ 54 ይሆናሉ፤ ነገር ግን በአጠራር ሰማኒያ አሃዱ (81) ይባል እንጂ ቁጥራቸው ከዚህ ያለፈ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል::

#### 2.1.2.2. የአዲስ ኪዳን የሥርዓት መጻሕፍት

ስለ አዲስ ኪዳን መጻሕፍት ዝርዝር ስንመለከት በሰፊው ቀኖና የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ቤተ ክርስቲያን ከ27ቱ በአጠቃላይ በክርስቲያኖች ዘንድ እስትንፋሰ እግዚአብሔር ያላቸው መሆናቸው ከታመነባቸው በተጨማሪ በሰፊው ቀኖና ስምንት የአዲስ ኪዳን መጻሕፍትን አክላ

ትቀበላለች፡፡ እነዚህን መጻሕፍት የሥርዓት መጻሕፍት በማለት የምትጠራቸው ሲሆን ዝርዝራቸውም የሚከተለው ነው[57]፡-

የሐዲስ ኪዳን የሥርዓት መጻሕፍት

1. ሥርዓተ ጽዮን (ስሲኖዶስ መጻሕፍት)
2. ትእዛዝ " "
3. ግጽው " "
4. አብጥሊስ " "
5. 1ኛ መጽሐፈ ኪዳን (የኢትዮጵያው?)
6. 2ኛ መጽሐፈ ኪዳን (የኢትዮጵያው?)
7. ቀሌምንጦስ (የኢትዮጵያው?)
8. ዲድስቅልያ (የኢትዮጵያው?)

በአጠቃላይ በዚህ በሰፊው ቀኖና ረገድ ከ46ቱ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በተጨማሪ 27ቱ የአዲስ ኪዳን የቀኖና መጻሕፍትና 8ቱ የሥርዓት መጻሕፍት ሲታከሉበት 35 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በድምሩ 81 መጻሕፍትን ትቀበላለች፡፡ በጠባቡ ቀኖና ግን ምንም ዓይነት ዳግማዊ የአዲስ ኪዳን የቀኖና መጻሕፍት እንዳሉ አታምንም፡፡ ከዚህም የተነሣ ሁሉም ዳግማዊ የቀኖና መጻሕፍት የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ናቸው፡፡

[57] ጠቅላይ ቤተ ክህነት፥ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነት ሥርዓተ አምልኮና የውጭ ግንኙነት፥ ገጽ 45



## 2.2. ኢትዮጵያ የመጻሕፍት ወዳጅ ወይስ... ?

### 2.2.1. የሌሎች ቅዱሳት መጻሕፍት ትውፊት በኢትዮጵያ

በዚህ ርዕስ ሥር ወደ ስፈረው ቁም ነገር ከማምራታችን በፊት ስለ ትውፊት ምንነት ለመረዳት መሞከሩ አስፈላጊ ነው፡፡ ትውፊት ማለት ከጥንት ጀምሮ በቤተክርስቲያን በኩል ቃል በቃል ሲነገር የመጣ በቃልም በጽሑፍም ከአበው ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የኖረና የሚኖር ማለት ነው፡፡ ... ስለዚህ ቅዱስ መጽሐፍና ትውፊት ይደጋገፋሉ ትውፊት መጽሐፍ ቅዱስን ይጠብቃል ይተረጉማል፤ ከመጽሐፍ ቅዱስ የቀረውን ይሞላል በማለት ይገልጹታል፡፡[58] እንግዲህ ትውፊት በቀኖና መጻሕፍት ላይ ይህንን አይነት ሥልጣን እንዳለው የሚናገሩለት ሲሆን በቃልም በጽሑፍም የሚተላለፍ መሆኑ መዘከሩ ደግሞ ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ በመሆኑ ላይ ትኩረት ይሰጥበታል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከላይ ከተዘረዘሩት ከቀኖና እና ከዳግማዊ የቀኖና መጻሕፍት በተጨማሪ ለመጻሕፍት ያላትን ልብ ባልተገደበ መልኩ ክፍተትን ታንጸባርቃለች፡፡ ይሁንና መሠረታቸው በብሉይና በሐዲስ ምሥጢራት ላይ ሆነው መደረስ እንዳለባቸው ባላት እምነት፡- «ከነዚህም ጋር (ከሠማንያ አሃዱ መጻሕፍት) የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን በብሉይና በሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት ላይ የተመሠረቱ የብሉያትና የሐዲሳትን ምሥጢራት አብራርተውና አጉልተው የሚገልጡ በልዩ ልዩ ቅዱሳን አበው የተደረሱ የሃይማኖት፥ የትምህርት የጸሎት መጻሕፍት

[58] ዝኒ ከማሁ፥ ገጽ. 47-48

